# የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን መንፈሳዊ ፍርድ ቤት መቋቋም አስፈላጊነትና ምቹ ሁኔታዎች

***ሙሉጌታ ጌጡ ፣ በላይነው አሻግሬ ፣ ዓለማየሁ ይስማው*****

## Abstract

In the early times, when the Orthodox Church was a state religion, the Ethiopian Orthodox Tewahido Church was able to extend its thoughts, values, cultures in all government affairs. Accordingly, the Church law, especially the *Fetha Negest* (The Law of Kings), became the governing law of the state since its introduction into Ethiopia; The judges have also been those who have knowledge of the Church dogmas, faith, orders and values. In this early period, the church had its own adjudicative organ, the ecclesiastical court, which adjudicate disputes that pertains to church affairs. At present, due to the separation of state and religion, the Church suffered from an external pressure since the regular/government courts are unable to preserve its interest, peace, and age-old contribution. This resulted in lack of just, fair and honest/integrity decision in a dispute between the Church and its workers, embarrassing its internal matters, adjudication of church disputes by judges who do not have knowledge of church's dogma, faith, orders, values. Some regular courts have decided that they do not have jurisdiction to entertain cases arising from the church, for example, employment disputes between the Church and its priests. Though the 1995 constitution of FDRE provides that a religious court will be established separate from the regular courts, the EOTC did not do much for the establishment of an ecclesiastical court. This article addresses issues concerning the ecclesiastical courts. Particularly, the article assesses the contribution of the establishment of ecclesiastical court to the Church, for national interest, the existence, or otherwise, of a legal framework for its establishment.

* ሙሉጌታ ጌጡ (ኤል ኤል ቢ፣ ኤል ኤል ኤም ፣ በሐረማያ ዩኒቨርስቲ የሕግ መምህርና የሕግ ኮሌጅ ተባባሪ ዲን)፤ በላይነው አሻግሬ (ኤል ኤል ቢ፤ በሐረማያ ዩኒቨርስቲ የሕግ ረዳት መምህር)፣ ዓለማየሁ ይስማው (ኤል ኤል ቢ፣ በሐረማያ ዩኒቨርስቲ የሕግ ረዳት መምህር) ናቸው። ይህ ጽሑፍ በነሐሴ 2003 ዓ.ም. ማኅበረ ቅዱሳን አዘጋጅቶት በነበረው ዐውደ ጥናት ላይ ቀርቦ የነበረ ሲሆን ከውይይቱ ተሳታፊዎች እና የጽሑፉ አራሚ ከነበሩት ፕሮፌሰር ጥላሁን ተሾመ የተሰጡትን አስተያየቶች ጨምሮ የቀረበ ነው። በዚህ አጋጣሚ ለሁሉም አካላት ልባዊ ምስጋናችንን እናቀርባለን።

# መግቢያ

የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ብሔራዊ ሃይማኖት በነበረበት በቀደመው ዘመን፤ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን (የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ) ያሏትን እሴቶች፣ ባሕሎችና አሰተምህሮዎች ሁሉ በብዙኃኑ የመንግሥት አሠራር ውስጥ ማስረጽ ችላ ነበር፡፡ ይህም የቤተክርስቲያኗን ሕግ (በተለይም ፍትሐ ነገሥት) የሀገሪቱ ሁሉ የበላይ ገዥ ሕግ፣ የፍርድ ቤት (ፍ/ቤት) ዳኞችም የቤተክርስቲያኗን ቀኖና፤ ሥርዐትና አሠራር የሚያውቁ እስከመሆን የተደረሰበት ጊዜ ነበር፡፡ በዚህ በቀደመው ዘመን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የራሷን ጉዳይ የሚዳኝ የፍትሕ አካል (መንፈሳዊ ፍ/ቤት) ነበራት፡፡[1] አሁን ባለንበት ዘመን ግን የሃይማኖትና መንግሥት መነጣጠልን ተከትሎ ቤተክርስቲያኗ ከሚደርሱባት የውጭ ጫናዎች አንዱ መደበኛዎቹ የፍትሕ አካላት የቤተክርስቲያኗን ሁለንተናዊ ጥቅም፣ ሠላም፤ የእምነትና አስተዳደር ነጻነት ለማስጠበቅ አለመቻል ነው፡፡ ይህም በአገልጋዮቿና በቤተክርስቲያኗ መካከል ለሚነሡ አለመግባባቶች ፍትሐዊ፣ ሚዛናዊና አርኪ ውሳኔን አለማግኘት፣ የቤተክርስቲያኗን ምስጢር በአደባባይ ማዋል፣ የበቤተክርስቲያኗ እሴትና አሠራር በማያውቁ ግለሰቦች መዳኘት ወዘተ አስከትሏል፡፡ በአንዳንድ ጉዳዮችም (ለምሳሌ፡- በካህናትና በቤተክርስቲያኗ መካከል የሚፈጠር የሥራ ክርክር) መደበኛ ፍርድ ቤቶች (ፍ/ቤቶች) የማየት ሥልጣን የለንም በማለታቸው የቤተክርስቲያኗ አገልጋዮች ፍትሕ የማግኘት መብታቸው ተጣቦ እናገኘዋለን፡፡[2]

የሕጎች ሁሉ የበላይ የሆነው ሕገ መንግሥት ከመደበኛ ፍ/ቤት በተጨማሪ ሃይማኖታዊ ፍ/ቤቶች ሊቋቋሙ እንደሚችሉ ቢጠቅስም[3] የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ ይህ ፍ/ቤት እንዲቋቋም ውጤታማ ሥራ አልሠራችም፡፡ ይህ ጥናታዊ ጽሑፍ በዚህ መንፈሳዊ ፍ/ቤት ዙሪያ የሚነሡ ጉዳዮችን የሚዳስስ ይሆናል። በተለይም ይኸው ፍ/ቤት ቢቋቋም ለቤተክርስቲያኗ ብሎም ለሀገር ደህንነትና ሰላም ያለው አስተዋጽኦ፣ የመቋቋሙን አስፈላጊነት፣ ለማቋቋም የሕገ መንግሥትና ሌሎች ሕጎች ድጋፍ መኖሩን ይዳስሳል። በተጨማሪም አሁን ባለው የመንግሥትና የፌደራሊዝም አወቃቀር ይህ ፍ/ቤት እንዴት ሊሠራ እንደሚችል፣ ተጠያቂነቱና ቁጥጥሩ፣ ሊመራበትና ሊተገብረው ስለሚገባው ሕጎች ለመረዳት ይረዳ ዘንድ የሌሎች ሀገሮች ልምድ ላይ ዳሰሳ ያደርጋል።

ጥናቱን በማድረግ ሂደት በተለይ የመረጃ ምንጮች እጥረት ነበር፡፡ በተያዘው ጉዳይ ላይ የተሠሩት ጽሑፎች እጅግ አነስተኛ ናቸው፡፡ በኢትዮጵያ ዘመናዊ የፍ/ቤት አሠራር ከተጀመረ ወዲህ የወጡትን ሕጎች ለመዳሰስ ተሞክሯል፡፡ ቢሆንም ግን በሁሉም ዓመታት የወጡትን ሕጎች ለማግኘት በብዙው ተቸግረን ነበር፡፡ የውጭ ሀገር የሃይማኖት ፍ/ቤቶችን ልምድ ለማግኘት የመረጃ መረብ ትልቁን ድርሻ ወስዷል፡፡

---

1 ይህም ለመጀመሪያ ጊዜ ቤተክርስቲያኗ የራሷ ሕግ ከተደነገገላት ከ፲፱፻፲፱ ዓ.ም ጀምሮ እንደነበረ መዛግብት ቢያስረዱም በተለይ በ፲፱፻፴፩ ዓ.ም የወጣው የቤ/ን አስተዳደር ሕግ ይህንን በግልጽ አስቀምጦት ይገኛል፡፡

2 ለምሳሌ የፌደራል ጠ/ፍ/ቤት ሰ/መ/ቁጥር 18418/98 በቤተክርስቲያኗ መደበኛ አገልጋይ ካህናትና በቤተክርስቲያኗ መካከል የሚፈጠር የሥራ ክርክርን ፍ/ቤቶች የማየት ሥልጣን የላቸውም በማለት ወስኗል፡፡

3 *የኢፌድሪ ሕገ መንግሥት* ዐዋጅ ቁጥር ፩/፲፱፹፯፤ አንቀጽ ፴፬/፭፡፡

 © ጥናትና ምርምር ማእከል፣ ማኅበረ ቅዱሳን

*ጥናታዊ ጽሑፉ በአራት ዋና ዋና ክፍሎች ተከፍሏል፡፡ የመጀመሪው ክፍል የመንፈሳዊ ፍ/ቤት ታሪካዊ አመጣጥን ይዳስሳል፡፡ ይህም ክፍል መንፈሳዊ ፍ/ቤቶች፤ በቤተክርስቲያኗ ውስጥ መሥራት ከጀመሩበት ጊዜ አንሥቶ አሁን እስካለንበት ዘመን ድረስ ያለውን የሚያካትት ሲሆን በሌሎች አገራት የመንፈሳዊ ፍ/ቤቶች ታሪካዊ አመጣጥንም በንጽጽር ይዳስሳል፡፡ ሁለተኛው ክፍል ደግሞ የመንፈሳዊ ፍ/ቤቶች በኢትዮጵያ ሕግ ሥርዐት ያላቸውን ቦታ ይገልጻል፡፡ ይህንንም ለማስረዳት የሕጎች የበላይ የሆነው ሕገ መንግሥቱ ስለ ሃይማኖታዊ ፍ/ቤቶች ምን እንደሚል፤ በተለይም ሕገ መንግሥቱ ከተቀበለው የሕግ ብዙሕነት አስተሳሰብ ጋር እያሰናሰለ ይመረምራል፡፡*

*በሦስተኛው ክፍል ደግሞ የመንፈሳዊ ፍ/ቤቶች መቋቋም የሚያስፈልግበትን ምክንያትና ሊያስገኘው የሚችለውን ጠቀሜታ ይተነትናል፡፡ በዚህ ክፍል ውስጥም የመንፈሳዊ ፍ/ቤቶች መቋቋም ጠቀሜታ ከሕጋዊ፣ ሃይማኖታዊ እንዲሁም ከሌሎች አቅጣጫዎች አንጻር ተዳሷል፡፡ በመጨረሻም ሃይማኖታዊ ፍ/ቤቶች በሌሎች ሀገራት እንዴት እየሠሩ እንደሆነ፣ ያላቸውን የሕግ ሽፋን፣ የፍ/ቤቶቹን አወቃቀር በተመለከተ የአሜሪካን፣ የሩሲያን የእስራኤልን እና በጥቂቱ የእንግሊዝን ልምድ በመውሰድ ይዳስሳል፡፡ በኢትዮጵያ ውስጥ ስላለው የሸሪአ ፍ/ቤትም ዳሰሳ ያደርጋል፡፡*

*ጥናታዊ ጽሑፉ በማጠቃለያ ሐሳቦች እና ባለድርሻ አካላት ሊወስዷቸው ስለሚገባቸው የመፍትሔ ሐሳቦች በመጠቆም ይጠናቀቃል፡፡ ይህ ጽሑፍ ስለ ጉዳዩ መነሻ ቢሆን እንጂ ምሉዕ አይደለም:: በተለይም ስለተግዳሮቱ፤ አወቃቀሩና ሓላፊነቱ፤ እንዴት ሊሠራ እንደሚችል ወዘተ አይዳስስም:: ስለሆነም ወደፊት በሚደረጉ ጥናቶችና ውይይቶች የሚዳብር ሲሆን የዚህ ጽሑፍ አቅራቢዎችም ቀጣይ ጥናቶችን በማድረግ ላይ ናቸው::*

## *፩ የመንፈሳዊ ፍ/ቤቶች ታሪካዊ ዳራ*

*ፍ/ቤቶች የሰውን መብት ለማስከበር ፣ ዜጎች መብቶቻቸው በተገፈፉባቸው ወይም ደግሞ መብቶቻቸው አልከበርላቸው ባለ ጊዜ ፣ ይህንን የመብት ጥሰት አይተው ሕግን ተርጉመው ፍትሕ ለመስጠት የሚያገለግሉ ተቋማት ናቸው::[4] እነዚህ ፍ/ቤቶች ስያሜያቸው ፣ አመሠራረታቸው የሚያዩት ጉዳይ የተለያየ ቢሆንም እንኳን፣ ዋና ዓላማቸውና ግባቸው ግን የመብት ጥሰት ባጋጠመ ጊዜ ፍትሕ መስጠት ነው ::[5]*

*በእንደዚህ ዓይነት ተግባር ላይ ለመሥራት የሚቋቋሙ የተለያዩ ፍ/ቤቶች አሉ:: የመጀመሪያውና ዋናው በተለይ በዘመናዊ የመንግሥት አስተዳደር፣ መንግሥት ያወጣቸውን ሕጎች ለመተርጐምና ፍትሕን ለማስፈን በመንግሥት የሚቋቋመው መደበኛ ፍ/ቤት ነው:: ይህ ፍ/ቤት ማንኛውም ወገን ቀርቦ ያለምንም ልዩነት መብቱን የሚያስከብርበት ወይም የሚጠይቅበት ነው:: እነዚህ ፍ/ቤቶች ቀደም ካሉት ጊዜያት አንሥቶ ሲሠራባቸው የኖሩ አሁንም በሁሉም የዓለማችን ክፍሎች የሚያገለግሉ ተቋማት ናቸው:: ነገር ግን እነዚህ ፍ/ቤቶች ፍትሕ የሚያሻውን ማንኛውም ዓይነት ጉዳይ ለማየት የማይችሉበት የተለያዩ ሁኔታዎች አሉ:: እንደዚህ በሆነ ጊዜ መንግሥት ከመደበኛ ፍ/ቤቶች በተጨማሪ ሌሎች ፍ/ቤቶችንም ያቋቁማል::[6]*

---

[4] Joanne Scott and Susan Sturm, "*Courts as Catalsysts: Re-thinkng the Judicial Role in New Governance,*" *Columbia Journal of European Law* Vol. 13, 2006, pp. 556-576.

[5] ዝኒ ከማሁ; Matias F. Travieso-Diaz and Armando A. Mus, *Courts of Special Jurisdiction in A Post-Transition Cuba,* Cuba in Transition · (ASCE 2005),pp. 320-321.

[6] ዝኒ ከማሁ::

ለምሳሌም ጊዜያዊ ፍ/ቤቶች፣ ልዩ ፍ/ቤቶች፣ አስተዳደራዊ ፍ/ቤቶች፣ የባሕል ፍ/ቤቶች፣ የሃይማኖት ፍ/ቤቶች ወዘተ በሕግ ያቋቁማል፤ ወይም ደግሞ እንዲቋቋሙ በሕግ ዕውቅና ይሰጣል፡፡[7] በዚህ ጽሑፍ የምንዳስሰው በተለየ ሁኔታ ከሚቋቋሙት አንዱ የሆነውን የሃይማኖት ፍ/ቤት በተለይም የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ መንፈሳዊ ፍ/ቤትን ነው፡፡

መንፈሳዊ ፍ/ቤቶች በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በተለያዩ ሀገሮች ረጅም ዘመናትን ያስቆጠሩ ተቋማት ናቸው፡፡ ለምሳሌ በሮም የመንፈሳዊ ፍ/ቤቶች ህልውና የሮማው ንጉሠ ነገሥት ታላቁ ቆስጠንጢኖስ ክርስትናን በ፬ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ከመቀበሉ በፊት የነበረ ነው፡፡[8] ክርስትና የሮማ ብሔራዊ ሃይማኖት ከሆነ በኋላ ደግሞ፤ መንፈሳዊ ፍ/ቤቶች በመደበኛው የፍትሕ ሥርዐት ተጠቃለሉ፡፡[9] በእንግሊዝ አገር ደግሞ ኖርማን የሚባሉ ሕዝቦች ሀገሪቷን ከተቆጣጠሩበት እ.ኤ.አ ከ፲፻፷፮ በኋላ እነዚህ መንፈሳዊ ፍ/ቤቶች ነበሩ፡፡[10] እንዲያውም ከ፲፻፸፪-፸፮ ዓ.ም ባሉት ጊዜያት እነዚህ ፍ/ቤቶች ከመደበኛ ፍ/ቤቶች ተለይተው ሲሠራባቸው ኑረዋል፡፡[11]

የፍ/ቤቶችን ታሪክ በኢትዮጵያ ስንመለከት የዘመናዊ ፍ/ቤት ውጥን የተጀመረው በ፲፱፻ ዓ.ም ዳግማዊ ዐፄ ምኒልክ የመጀመሪያውን የሚኒስትሮች ም/ቤት ባቋቋሙበት ጊዜ ነበር፡፡[12] ከዚህ በፊት ግን ፍትሕን የሚያስተዳድረውና ጉዳዮችም እልባት ይሰጣቸው የነበረው በባሕላዊ የዳኝነት ሥርዐት (በጎሳና አካባቢ መሪዎችና ሹሞች)፣ በነገሥታት እንዲሁም በዐፄዎች ነበር፡፡ ከ፲፱፻ ዓ.ም. ወዲህ ግን የፍ/ቤት አከፋፈሉም የአፈር ዳኛ፣ የአካል ዳኛ፣ ሻለቃ ፍ/ቤት፣ አፈንጉሥ፣ ዙፋን ችሎት ይባል ነበር፡፡[13] ከ፲፱፻ ዓ.ም. ወዲህ መደበኛና መደበኛ ያልሆኑ ፍ/ቤቶች በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ፍርድ የመስጠት ሥልጣን ነበራቸው፡፡ እንዲህ ዓይነት የዳኝነት አስተዳድርም የመጀመሪያው የፍትሕ አስተዳደር ዐዋጅ ቁጥር ፪/፲፱፻፴፬ ከወጣ ወዲህ ሲሠራበት ነበር፡፡

ወደ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን (ኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ) መንፈሳዊ ፍ/ቤት ስንመለስ ደግሞ ቅድመ ፲፱፻፷፰ ዓ.ም በሃይማኖት መሠረት የተፈጸመ ጋብቻ ፍቺን፣ የቤተክርስቲያንን አስተዳደር፣ የቤተክርስቲያን ንብረቶችን በተመለከተ የሚነሡ ጉዳዮች ለመንፈሳዊ ፍ/ቤቶች ይቀርቡ ነበር፡፡ [14] ፍ/ቤቶቹ በአዲስ አበባና በሌሎች ሀገረ ስብከቶችም የተቋቋሙ ሲሆን የሚያስችሉትም እጨጌዎች ነበሩ፡፡ የይግባኝ ሥርዐትም እንደነበረ የሚታወቅ ነው፡፡[15] በተጨማሪም የገዳማት አበምኔቶችና የአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት አለቆች ቀለል ያሉ የፍትሐ ብሔር እና የወንጀል ጉዳዮችን የማየት ሥልጣን የነበራቸው ሲሆን ከዚህ ውሳኔ ላይም ይግባኝ ይጠየቅ ነበር፡፡

---

[7] Friederike Henke, *Specialized Court System- Comparative Paper Analyzing the Possibilities of Implementing a Specialized Court System in India* (2005), p. 3.

[8] "Ecclesiastical Courts." Microsoft Encarta [DVD]. (Redmond, WA, 2009)

[9] James Findley, *The Debate Over Nonlawyer Probate Judges: A Historical Perspective,* Alabama Law Review, Vol. 61:5, (2010); pp.1143

[10] Noel Cox, *The influence of the Common Law on the Decline of the Ecclesiastical Courts of the Church of England,* p. 6; Noel Cox, *The Symbiosis of Secular and Spiritual Influences upon the Judiciary of the Anglican Church in Newzealand,* Deakin Law Review, Volume 9 NO 1, (2004); pp. 2-7.

[11] ዝኒ ከማሁ፡፡

[12] Aberra Jembere, *Legal History of Ethiopia 1434-1974: Some Aspects of Substantive and Procedural Laws* (Erasmus University, 1977); p. 217.

[13] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 214-218፡፡

[14] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 227፡፡

[15] ዝኒ ከማሁ፡፡

ፍትሐ ነገሥቱም አሠራራቸውን፣ የዳኞችን አሿሿም፣ የምስክሮችን ሁኔታና ሌሎች ሥነ ሥርዐቶችን በሚገባ ደንግጓል ።[16]

እነዚህ መንፈሳዊ ፍ/ቤቶችም ኢትዮጵያ ከጣሊያን ቁጥጥር ነጻ ከወጣች በኋላም ለጥቂት ጊዜ ሲሠራባቸው ቆይተዋል፡፡ በ፲፱፻፴፮ ዓ.ም የቤተ ክርስቲያን ደንብ የሚል ሕግ ወጥቷል፡፡ ይህ ደንብ ቤተክርስቲያኗ የራሷን ጉዳዮች የምታይበት ፍ/ቤት እንዳላት ይናገራል፡፡ የደንቡ አንቀጽ ፲ እንደሚከተለው ይነባባል፡፡

> *ቤተክርስቲያኗ ምእመናንን በንስሐ የምትሠራበት፣የምትቀጣበት የግል ዳኝነት አላት፡፡ ዳግመኛም የውስጥ ቤተሰቦቿ የሆኑ ካህናትን በመንፈሳዊ ተግሣፅ እያስማማች ታስተዳድራለች፡፡ በዓለማዊው ዳኝነት ግን በመንግሥት የሚሾሙ ዳኞች እየጠበቁ ያስተዳድራሉ፡፡ ለዓለማዊ ዳኝነት የሚበቁ ሰዎችን የመንፈሳዊ ጉባኤ ለማቅረብ ይችላል፡፡ የሚሾሙትም በንጉሠ ነገሥቱ ነው፡፡*

ይህንን የደንቡን አንቀጽ ስንመለከት ቤተክርስቲያኗ በሁለት ዐቢይ ጉዳዮች ላይ የዳኝነት ሥልጣን እንዳላት እንረዳለን፡፡ የመጀመሪያው ሙሉ በሙሉ መንፈሳዊ ጉዳዮችን በተ መለከተ ሲሆን በዚህም ላይ (እንደ አንቀጹ አገላለጽ) የግል ዳኝነት አላት፡፡ ይህም ማለት እንደዚህ ዓይነት ጉዳዮችን በተመለከተ ከቤተክርስቲያኗ ውጭ ሌላ አካል (ፍ/ቤት) የማየትና የመዳኘት ሥልጣን እንደሌለው ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ ዓለማዊ ዳኝነትን የተመለከተ ነው፡፡ እንደዚህ ዓይነት ጉዳዮችን የሚዳኙ ዳኞች በመንግሥት ወይም በመንፈሳዊ ጉባኤ አቅራቢነት በንጉሠ ነገሥቱ ይሾማሉ፡፡

በዚህ ደንብ መሠረትም በአዲስ አበባ የመንፈሳዊ ከፍተኛ ፍ/ቤት እና ጠቅላይ ፍ/ቤት ተቋቁመዋል፡፡[17] የዳኝነት ሥልጣናቸውም ከላይ በተጠቀሰው አንቀጽ ፲ መሠረት ከተለያዩ የሀገረ ስብከት ፍ/ቤቶች ለሚመጡ ጉዳዮች ይግባኝ የማየት ሥልጣን አላቸው፡፡ በእያንዳንዱ ፍ/ቤት ሦስት ዳኞች ያስችላሉ፤ ክርክሩም የሚሰማ በግልጽ ነበር፡፡[18]

ይህን ደንብም ስንመለከተው በኢትዮጵያ ዘመናዊ ሕግ ውስጥ ለቤተክርስቲያኗ መንፈሳዊ ፍ/ቤቶች ዕውቅናና ከመደበኛው ፍ/ቤቶች ጎን ለጎን የመዳኘት ሥልጣን የሰጠ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ ለመጀመሪያ ጊዜ ለሸሪአ ፍ/ቤቶችም በዘመናዊ ሕግ ውስጥ ዕውቅና የሰጠና እንዲሠሩ ያቋቋማቸው ዐዋጅ በ፲፱፻፴፩ ዓ.ም ወጥቷል፡፡ ከዚያ በኋላ ማሻሻያ እየተደረገላቸውና እንደገና ተደራጅተው እየሠሩ ነው፡፡[19]

---

[16] ፍትሐ ነገሥቱ መንፈሳዊ ፍ/ቤትን ስለማቋቋም በግልጽ ያለው ነገር የለም፡፡ ነገር ግን በመንፈሳዊ ቤተክርስቲያኗ ጉዳዮች ላይ ሙሉ የዳኝነት ሥልጣን፣ ሌሎች አማኞችን የሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ደግሞ የፍቃድ ዳኝነት (ከመኳንንት ፍርድ ጋር ጎንለጎን ይሠራል) ሊኖራት እንደሚችል ይጠቁማል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በተለይ የፍትሐ ነገሥቱ አንቀጽ ፵፫ ቤተክርስቲያኗ በሚኖራት ፍ/ቤት ሊሾሙ ስለሚገባቸው ዳኞች ዕውቀት፣ አሿሿም፣ ጠባይ፣ ስለዳኛ አሻሻር፣ ስለዳኝነት አገላለጽ፣ ቦታ፣ የሥራ ቀን፣ ስለማስረዳት ሸክም፣ ስለእርቅ፣ የምስክር ዓይነት፣ አመሰካከር ወዘተ በደንብ ደንግጎ ይገኛል፡፡ ፍትሐ ነገሥት ሥጋዊ ወመንፈሳዊ፣ በተስፋ ገብረሥላሴ ማተሚያ ቤት፣ ፲፱፻፺፪ ዓ.ም.፣ አዲስ አበባ፣ አንቀጽ ፵፫። (የእንግሊዝኛውን ቅጂ *THE FETHA NAGAST: The Law of the Kings*, Translated from the Ge’ez by Abba Paulos Tzadua, edited by Peter L. Straus, Carolina Academic Press፣ 2009.)

[17] ከላይ የተጠቀሰው የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር ፲፪፣ ገጽ ፪፻፴

[18] ዝኒ ከማሁ፡፡

[19] የቃዲዎች ፍርድ ቤት የተቋቋመበት ዐዋጅ ቁጥር ፲፪/፲፱፻፴፩፤ ፩ኛ ዓመት፣ ቁጥር ፪፣ ዐዋጅ ቁጥር ፩፻፹፰/የቃዲዎች ፍርድ ቤት የተቋቋመበት ዐዋጅ ቁጥር ፲፪/፲፱፻፴፩፤ ፩ኛ ዓመት፣ ቁጥር ፪፣ ዐዋጅ ቁጥር ፩፻፹፰/፺፪፡፡

ነገር ግን በ፲፱፻፶፪ ዓ.ም የወጣው የፍትሐ ብሔር ሕግ *(ከዚህ በኋላ "ፍ/ብ/ሕ" እየተባለ የሚጠቀስ)* ዋና ዓላማው በሀገሪቱ ውስጥ ወጥ የሆነ የሕግ ሥርዐት እንዲኖር ማድረግ ስለነበር በሀገሪቷ ውስጥ የሚገኝ ማንኛውንም ዓይነት ሕግ በፍትሐ ብሔር ሕጉ ለመተካት ሞክሯል፡፡ ዓላማውን ለማሳካት ፍትሐ ብሔር ሕጉ በሀገሪቱ ውስጥ የነበሩ ልማዶችን፣ ባሕሎችን፣ ሃይማኖታዊ እሴቶችን እንደየአግባብነታቸው በሕጉ ውስጥ እንዲካተቱ አድርጓል:: በተጨማሪም የታሰበው አንድ ወጥ የሕግ ሥርዐት እንዲኖር ለማድረግ ፍትሐ ብሔር ሕጉ በቁጥር ፫ሺ፫፻፵፯ ላይ ማንኛውም ልማዳዊ ወይም ማናቸውም ሕጎች በፍትሐ ብሔር ሕጉ እስከተካተቱ ድረስ መሻራቸውን ይናገራል:: የሕጉ ሙሉ ቃል እንደዚህ ይላል::[20]

> *ግልጽ የሆነ ተቃራኒ ድንጋጌ ከሌለ በቀር፤ በዚህ በፍትሐ ብሔር ሕግ ውስጥ ለተመለከቱት ጉዳዮች ከዚህ በፊት በልማድ ወይም ተጽፈው ይሠራባቸው የነበሩት ደንቦች ሁሉ፤ ይህ የፍትሐ ብሔር ሕግ ሰለተተካ ተሽረዋል::*

ከዚህ የሕጉ ቁጥር መረዳት እንደሚቻለው ፍ/ብ/ሕጉ ለባሕላዊ ፣ ሃይማኖታዊ፣ መደበኛ ሕጎች በፍ/ብ/ሕጉ እስከተካተቱ ድረስ ምንም ዓይነት ቦታ እንዳልተሰጣቸው ነው:: ለእነዚህ ሕግጋት ቦታ አልሰጠም ማለት እነዚህን ሕግጋት ለሚያስፈጽሙ ፍ/ቤቶችም ቦታ አልሰጠም ማለት ነው:: ምክንያቱም ልማዳዊ ሕጎችን የሚተገብሩት ልማዳዊ ፍ/ቤቶች፣ ሃይማኖታዊ ሕጎችን የሚተረጉሙት ሃይማኖታዊ ፍ/ቤቶች፣ መደበኛ ሕጎችን ደግሞ መደበኛ ፍ/ቤቶች በመሆናቸው ነው፡፡ ልማዳዊ ፍ/ቤቶች ሃይማኖታዊ ሕግን መተርጐም አይችሉም፡፡ እንደዚሁም ሃይማኖታዊ ፍ/ቤቶች ባሕላዊ ወይም መደበኛ ሕጎችን መተርጐም አይችሉም::

ምንም እንኳ የፍ/ብ/ሕ ቁጥር ፫ሺ፫፻፵፯ ከላይ እንደሚለው ቢደነግግም ተግባራዊነቱ የመነጋገሪያ ጉዳይ ነበር::ይኸውም የፍትሐ ብሔር ሕጉ ልማዶችን፣ ቀደም የተጻፉትን ሕጎች በግልጽ የሻረ ቢሆንም፤ ፈጽሞ ሊያስወግዳቸው ግን ስላልቻለ ነው፡፡ ይልቁንም ብዙውን ጊዜ ሕዝቡ ሲተዳደርና ሲገዛ የነበረው ይዟቸው በኖረው ልማዳዊ ሕጎች ነበር፡፡[21] ለምሳሌም የሸሪአ ፍ/ቤቶች የ፲፱፻፶፪ቱ ፍ/ብ/ሕ ከወጣ በኋላም ሲሠራባቸው ነበር::

በአሁኑ ወቅት በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ ውስጥ የተለያዩ ዓይነትና ይዘት ያላቸው ክርክሮች ይነሣሉ:: ለምሳሌ የንብረት ፣የጋብቻና ፍቺ፣ የክህነት ፣የሥነ-ምግባር፣ የሥራ ክርክር ወዘተ:: ቤተክርስቲያኗን የሚመለከቱት እነዚህ ጉዳዮች እንዴት ነው እየተዳኙ ያሉት? በቤተክርስቲያኗን ውስጥ ለዚህ ጉዳይ የተቋቋመ አካል አለን? የሚለውን በአጭሩ ለማየት እንሞክራለን፡፡

ቤተክርስቲያኗ ምንም እንኳ በመደበኛ ሕግ የተቋቋመ ፍ/ቤት ባይኖራትም ክርክሮችን የምታስተናግድበትና ፍትሕ የምትሰጥበት አካል አላት:: ቤተክርስቲያኗን ከአጥቢያ ቤ/ክ እስከ ጠቅላይ ቤተ ክህነት የምትመራበትና የምትተዳደርበት ሕግ (ቃለ ዓዋዲ) አላት:: ይህ ቃለ ዓዋዲ ነው ጉዳዮችንና ክርክሮችን አይቶ የሚወስነውን የቤተክርስቲያኗን አካል ያቋቋመው::

በዚህ ሕግ (ቃለ ዓዋዲ) መሠረት የሕግና ሥነ ሥርዐት ክፍል ተቋቁሟል::[22] ይህ ቃለ ዓዋዲ የቤተክርስቲያኗን መዋቅር ከአጥቢያ ቤ/ክ እስከ መንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ቤተክህነት ሲያቋቁም በየደረጃው ባሉት እርከኖች ደግሞ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ እና አስተዳደር ጉባኤ /ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ/ ጨምሮ አቋቁሟል::

---

[20] የፍ/ብ/ሕ ቁጥር ፫ሺ፫፻፵፯ ዐዋጅ ቁጥር ፩፻፷፭/፲፱፻፶፪ ዓ.ም፡፡

[21] John W. Van Doren, *Positivism and the Rule of Law, Formal Systems or Concealed Values: A Case Study of the Ethiopian Legal System,* Journal of Transnational Law & Policy, 165, 1994. ይህ ማለት ግን ሁሉም ከፍትሐ ብሔሩ በፊት የነበሩ ሕግጋት ተሽረዋል ማለት አይደለም፡፡ በተለይ በፍትሐ ብሔር ሕጉ ያልተካተቱ ጥቂት ነገሮች እንዳሉ ልብ ይሏል፡፡ አንዳንዶቹም እስከአሁን ድረስ እየተሠራባቸው ነው፡፡

[22] የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ/ ቃለ ዓዋዲ፣፲፱፻፺፩፣አንቀጽ ፳፬

በዚህም መሠረት ሕግ ነክ ጉዳዮችንና ክርክሮችን የሚመለከተው በየደረጃው ያለው የመንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ ነው:: ይህ አስተዳደር ጉባኤ በየእርከኑ የተቋቋመ ሲሆን የመጀመሪያ እና ይግባኝ የማየት ሥልጣን አለው::

በዚህም መሠረት የአጥቢያ ቤ/ክ/ ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ ጋብቻን፣ ሥልጣነ ክህነትን፣ የምስጢራተ ቤ/ክ ጉዳዮችን[23] እንዲሁም አስተዳደራዊ ጥፋቶችን አይቶና መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል::[24] በአጥቢያው ቤ/ክ ባለው የሕግና ሥነ ሥርዐት ኮሚቴ የሚሰጡ የዲሲፒሊን ውሳኔዎችን የማየት ሥልጣንም አለው::[25] በአጥቢያው ቤ/ክ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ በተሰጠው ውሳኔ ቅሬታ ያለው አካል ጉዳዩን ለወረዳ ቤተክነት መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ በይግባኝ ሊያቀርብ ይችላል::[26] በወረዳው ቤተክህነት የተሰጠው ውሳኔ ቅሬታ ካለ ደግሞ ጉዳዩ ለሀገረ ስብከት አስተዳደር ጉባኤ በይግባኝ ሊቀርብ ይችላል::[27] አሁንም ቢሆን በሀ/ስብከት አስተዳደር ጉባኤ ውሳኔ ቅር የተሰኘ ቢኖር ጉዳዩን ለመንበረ ፓትርያርክ ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ በይግባኝ ማቅረብ ይችላል::[28] ነገር ግን ከታችኞቹ የቤተክርስቲያኗ መዋቅሮች በይግባኝ የሚሔዱ ወይም በመ/ፓ/ጠ/ቤ/ክህነት በመጀመሪያ ደረጃ የሚቀርቡ ጉዳዮች በፓትርያርኩ አማካኝነት በቋሚ ሲኖደስ ወይም በቅ/ሲኖደስ ጉባኤ እንዲታዩና ውሳኔ ሊያገኙ እንደሚችሉ ቃለ ዓዋዲው በአንቀጽ 52(3) ሥር አስቀምጧል::

ምንም እንኳ ቃለ ዓዋዲው ፍትሕና ዳኝነት የሚሰጠውን አካል (አስተዳደር ጉባኤውን) ከአጥቢያ ቤ/ክ እስከ መ/ፓ/ጠ/ቤ/ክህነት ድረስ ባለው መዋቅር ውስጥ ቢያቋቁምም ከችግሮች ሊያመልጥ አልቻለም:: ለምሳሌ በመጀመሪያ ደረጃ ይህ አካል በመንግሥት (መደበኛ) ሕግ ዘንድ ዕውቅና አለማግኘቱ ነው:: ይህም በበኩሉ የአስተዳደር ጉባኤው የሚሰጣቸው ውሳኔዎች ከቤተክርስቲያኗ ውጭ ባሉ አካላት ያለው ተቀባይነት አጠያያቂ ነው:: በመቀጠልም አስተዳደር ጉባኤው የሚያያቸው/የሚዳኛቸው ጉዳዮች ሁሉም ተለይተው በዝርዝር አልተቀመጡም:: በመጠኑም ቢሆን በተጠቀሱት ጉዳዮች (ለምሳሌ፡ አስተዳደራዊ ጉዳዮች) እንኳ አስተዳደር ጉባኤው ጉዳዩን ለማየት የሚያስችል ሙሉ (Exclusive) ሥልጣን አለው ለማለት አያስደፍርም:: ከዚህ በተጨማሪም አስተዳደር ጉባኤው ሊተገብራቸው ስለሚችሉ መሠረታዊና የሥነ ሥርዐት ሕጎች በቃለ ዓዋዲው ውስጥ አልተጠቀሰም::

ከላይ ከተጠቀሱት ክፍተቶች በተጨማሪ ቃለ ዓዋዲው ስለይግባኝ ሥርዐት ግልጽነት ይጎድለዋል:: ይህን ለማብራራት ያክልም ለምሳሌ የተክሊል ጋብቻን፣ ሥልጣነ ክህነትን፣ የምስጢራተ ቤ/ክ ጉዳዮችን በተመለከተ የሚያየው በአጥቢያው ያለው የካህናት ጉባኤ ነው ይላል:: ካልተቻለም የሚመለከተው የበላይ አካል ነው ይላል:: ይህ የበላይ አካል ማን ነው? የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያኑ ወይም የወረዳ ቤተ ክህነት አስተዳደር ጉባኤ ስለመሆኑ ወይም ደግሞ ሌላ የካህናት ጉባኤ ስለመኖሩ አይናገርም:: በተጨማሪም በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያኑ ያለው የሕግና ሥነ ሥርዐት ክፍል የሚወስናቸው የዲሲፕሊን ጉዳዮች በይግባኝ ለአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ጉባኤ ይቀርባሉ:: ይህ ደግሞ በአንድ የቤተክርስቲያኗ እርከን ውስጥ የይግባኝ ሥርዐት እንዲኖር የሚፈቅድ ነው:: ከሁሉም በላይ ደግሞ ቃለ ዓዋዲው የሥራ አስፈጻሚውን እና የሕግና ፍትሕ አካሉን የፍ/ቤትን ሥልጣን በማደባለቅ ለአስተዳደር ጉባኤው (ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው) ሰጥቶታል:: ይህ ማለት ደግሞ አስተዳደር ጉባኤው የሥራ አስፈጻሚነትና የዳኝነት ሥልጣንን ደርቦ ስለሚሠራ ፍ/ቤቱ ራሱን የቻለ ነው ለማለት አይቻልም::

---

[23] እነዚህን ጉዳዮች የማየትና የመወሰን ሥልጣን የካህናት ጉባኤው ነው:: ቃለ ዓዋዲ ፣፲፱፻፺፩ ዓ.ም አንቀጽ ፲፪(፬)
[24] ዝኒ ከማሁ፣አንቀጽ ፲፪(፳፬)
[25] ዝኒ ከማሁ፣አንቀጽ ፲፪(፳፫)
[26] ዝኒ ከማሁ፣አንቀጽ ፳፬(፩)
[27] ዝኒ ከማሁ፣አንቀጽ ፵፬(፫) እና ፳፬(፪)
[28] ዝኒ ከማሁ፣አንቀጽ ፶፩(፫)

## ፪ መንፈሳዊ ፍ/ቤቶች በአሁኑ የኢትዮጵያ ሕግ ሥርዐት ያላቸው ቦታ

በ፲፱፻፹፯ ዓ.ም የወጣው የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲዊ ሪፐብሊክ (*ከዚህ በኋላ "ኢ.ፌ.ዴ.ሪ" እየተባለ የሚጠቀስ*) ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፳፯ ማንኛውም ሰው የሃይማኖት ነጻነት እንዳለው ይናገራል::[29] በዚህ የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ መሠረትም የሃይማኖት ነጻነት በመታወጁ ማንኛውም ሰው የመረጠውን ሃይማኖት ወይም እምነት የመያዝ ወይም የመቀበል፣ ሃይማኖቱንና እምነቱን ለብቻ ወይም ከሌሎች ጋር በመሆን በይፋ ወይም በግል የማምለክ፣ የመከተል፣ የመተግበር፣ የማስተማር ወይም የመግለጽ መብት አለው:: በተጨማሪም ሕገ መንግሥቱ በአንቀጽ ፲፩ ላይ የመንግሥትና የሃይማኖት መለያየት የሚለውን መርሕ በግልጽ በመደንገጉ በሕግ ያቋቋመው ብሔራዊ ሃይማኖት የለም፤ መንግሥትና ሃይማኖት የተለያዩ መሆናቸውን በመግለጹ፡፡[30] ይህ ማለት ግን መንግሥት ስለሃይማኖት ዕውቅና አይሰጥም ማለት አይደለም:: ሕገ መንግሥቱ ያስቀመጠው ብሔራዊ ሃይማኖት እንደማይኖር እንጂ ሃይማኖት አይኖርም ማለት አይደለም:: አንቀጽ ፳፯ን በትኩረት ስንመረምረውም የተለያዩ ሃይማኖቶች ሊኖሩ እንደሚችሉ ያስረዳል::

በዚህም መሠረት የኢትዮጵያ ሕግ ፍጹም የሆነ የመንግሥትና የሃይማኖት መለያየትን (strict secularism) የሚከተል አይደለም:: እንዲያውም በአንዳንድ ጉዳዮች /በተለይ በግልና በቤተሰብ ሕግ/ ላይ ተከራካሪ ወገኖች ከፈቀዱ ሃይማኖታዊና ባሕላዊ ፍ/ቤቶች የመዳኘት ሥልጣን ሊኖራቸው እንደሚችል ደንግጎ እናገኘዋለን::[31] ስለዚህ በዚህ ጉዳይ ላይ የኢትዮጵያ ሕግ አቋም በሕገ መንግሥት ያልታወቀ ብዙኀነት (non constitutional pluralism) የሚለውን ሥርዐት የያዘ ነው:: በጠቅላላው ደግሞ ኢትዮጵያ የሕገ ብዙኀነትን መርሕ በሕግ ሥርዐቷ ውስጥ አካታ እንደያዘች የሚያረጋግጥ ድንጋጌ ነው፡፡

---

[29] በደርግ ዘመን የተደረገ ዕድገት እንዳለ ለመመልከት ያደረግነው ፍተሻ በመረጃ እጦት ምክንያት ብዙ ፍሬ አላስገኘም:: ነገር ግን በዘመኑ መጨረሻ አካባቢ (በ፲፱፻፹ዓ.ም.) የታወጀው ሕገ መንግሥት ስለመንግሥትና ሃይማኖት መነጣጠል እንዲሁም ስለዳኝነት ሥልጣን በሚደነገግበት አንቀጾች መንፈሳዊ ፍ/ቤቶችን በተ መለከተ በግልጽ የደነገገው ጉዳይ አልነበረም:: ነገር ግን የዳኝነት ሥልጣን «*በጠ/ፍ/ቤት፣ የአስተዳደር አካባቢዎችና የራስ ገዝ አካባቢ ፍ/ቤቶችና የሌሎች በሕግ የሚቋቋሙ ፍ/ቤቶች ብቻ*» መሆኑን ደንግጓል፡፡ ስለዚህም መንፈሳዊ ፍ/ቤትም ቢሆን በሕግ እስከተቋቋመ ድረስ ሥልጣን እንዳይኖረው በሕገ መንግሥት ደረጃ አልተከለከለም ነበር ወደሚል መደምደሚያም ሊያደርሰን ይችላል፡፡ ነገር ግን በዘመኑ የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ መንፈሳዊ ፍ/ቤት በሕግ አልተቋቋመም ነበር፡፡ አንቀጽ ፵፯ እና ፩፻፣ ዐዋጅ ቁ ፩/፲፱፻፹ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት።

[30] Veit Bader, *Religious Diversity and Democratic Institutional Pluralism* (University of Amsterdam, 2003); pp. 269-271; የሌሎች ሀገራትን ልምድ ስናይ ግን ሃይማኖትን በሕገ መንግሥቶቻቸውና ሌሎች ሕግጋት ውስጥ በተለያየ መልኩ አስቀምጠውት እናገኛለን:: አንዳንድ ሀገራት አንድ ሃይማኖት በሕገ መንግሥት ዕውቅና ሲሰጡ (ግሪክ፣ ሰርቢያና እስራኤል) ሌሎቹ ደግሞ በሕግም ሆነ (de jure) በአሠራር (de facto) አንድ ሃይማኖት በሕገ መንግሥት ያቋቁማሉ (እንግሊዝ፣ ስኮትላንድ፣ የስካንዲኔቪያን ሀገሮች):: ሌሎች ሀገራት ደግሞ በሕገ መንግሥታቸው ከአንድ በላይ ሃይማኖት ዕውቅና ሲሰጡ (ለምሳሌ በፊንላንድ /ሁለት የመንግሥት ሃይማኖቶች የሉተራንና የኦርቶዶክስ ቤ/ክ ተቋቁመዋል)፣ በሕገ መንግሥት ሳያቋቁሙ ነገር ግን በተወሰኑ የሕግ ዘርፎች ላይ የሕግን ብዙኀነት የሚከተል፣ በሕግ ወይንም ደግሞ ያለ ሕግ የተለያዩ ሃይማኖቶችን ተቋማዊ ብዙኀነት የሚቀበል (በኔዘርላንድ /ከ፲፱፻፹፫ ወዲህ/፣ በቤልጂየም፣ በሕንድ እና በጀርመን)፤ በመጨረሻም ደግሞ የሃይማኖት እና የመንግሥት ፍጹም መለያየትን የሚያቀነቅኑና ምንም ዓይነት ሃይማኖት በሕገ መንግሥት የማያቋቋሙ ዕውቅና የማይሰጡ/ አሉ (አሜሪካና ቱርክ)::

[31] ኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግሥት፣ ዐዋጅ ቁጥር ፩/፲፱፻፹፯፣ አንቀጽ ፴፬፡፡

የሕገ ብዙኀነት ማለት መንግሥት ከሚያወጣቸው መደበኛ ሕጎች ጐን ለጐን ሌሎች ዓይነት ሕጎች መኖራቸውን ዕውቅና የሚሰጥ ወይም እንዲሠራባቸው የሚፈቅድ መርሕ ነው::[32] ሰው የሚገዛው መንግሥት ባወጣው ሕግ ብቻ እንዳልሆነ ያብራራል:: ይህ መርሕ የተመሠረተባቸው የራሱ የሆኑ ጽንሰ ሐሳቦች አሉት:: ከእነዚህም መካከል የተለያዩ ባሕላዊ፣ ሃይማኖታዊ፣ ልማዳዊ ሕጎች ከመደበኛ ሕጎች ጐን መኖራቸው ነው:: መርሑ ባሕል፣ ሃይማኖት፣ ልማድ ከቦታ ቦታ ከጊዜ ጊዜ ሊለያይ እንደሚችል ስለሆነም ዕውቅና መሰጠት እንዳለበት ያስረዳል::[33]

የመዳኘት ሥልጣንን በተመለከተ ደግሞ የሕገ ብዙኀነት መርሕ የመዳኘት ሥልጣን ከመደበኛ ፍ/ቤቶች በተጨማሪ ሌሎች አካላትም የመዳኘት ሥልጣን ሊሰጣቸው እንደሚገባ ያስገነዝባል :: የተለያዩ ሃይማኖታዊ፣ ባሕላዊ፣ ልማዳዊ ሕጎች ካሉ እነዚህን ለማስተዳደርና ለመዳኘት የሚችሉ ሃይማኖታዊ፣ ባሕላዊ፣ ልማዳዊ ፍ/ቤቶችም ሊኖሩ እንደሚገባ ይናገራል:: ይህ መርሕም ዓለም አቀፋዊነትን እያገኘ መጥቷል፡፡[34]

የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥትም ይህንን መርሕ በመገንዘብ፣ የኢትዮጵያን ነባራዊ ሐቅ ማለትም ኢትዮጵያ የተለያዩ ሃይማኖቶች፣ ብሔሮች፣ ልማዶች፣ ባሕሎች የሚገኙባት መሆኗን ከግንዛቤ አስገብቷል:: በዚህም መሠረት ለእነዚህ ልዩነቶች በሕገ መንግሥቱ ቦታ ለመስጠት የሕዝቦችን መብት ለማስጠበቅ እንዲሁም ደግሞ ለእነዚህ ነገሮች እውቅና መስጠት የሚያስገኘውን ሕጋዊ፣ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ባሕላዊ እና ሌሎችም ጥቅሞችን ከግንዛቤ በማስገባት የሕግ ብዙሕነትን ተቀብሏል:: ይህንንም የሕገ መንግሥቱን አቋም ከተለያዩ የሕገ መንግሥቱ አንቀጾችና በአጠቃላይም ከሕገ መንግሥቱ አወቃቀር መረዳት ይቻላል::

አስቀድሞ እንደተገለጸው በ፲፱፻፹፯ ዓ.ም የወጣው የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፳፯ ማንኛውም ሰው የሃይማኖት ነጻነት እንዳለው ይናገራል:: ይህ ሕገ መንግሥት ቀደም ካሉት ሕገ መንግሥቶችም ሆነ ከፍ/ብ/ሕጉ ለየት የሚያደርገው ልዩ መገለጫዎች እንዳሉት ከተለያዩ የሕገ መንግሥቱ አንቀጾች መረዳት እንችላለን::አንቀጽ ፳፯ የሃይማኖት ልዩ መገለጫዎች እንዳሉት ነጻነትን ሲያውጅ በአንቀጽ ፴፬/፭/ ደግሞ ዜጐች የግልና የቤተሰብ ጉዳዮችን በተመለከተ ራሳቸው ከፈቀዱ በሃይማኖት ወይም በባሕል ሕጐች መሠረት መዳኘትን እንደማይከለክል አስቀምጧል:: በሌላ አገላለጽ አንቀጽ ፴፬/፭/ የሃይማኖት ወይም የባሕል ሕጐች እንዳሉና በሥራ ላይ ሊውሉ እንደሚችሉ ዕውቅና ሰጥቷል:: የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ የራሷ የሆነ ሕግና ሥርዐት ስላላት መንፈሳዊ ጉዳዮችን በተመለከተ የምትዳኝበት መንፈሳዊ ሕግ፣ ዓለማዊ ጉዳዮችን በተ መለከተም የምትዳኝበት ዓለማዊ ሕግ አውጥታ ስትገለገልበትና ስታገለግልበት ኑራለች (ፍትሐ ነገሥቱን ዋቢ ማድረግ ይቻላል)::

ሕገ መንግሥቱ በሃይማኖት ወይም በባሕል ሕጐች መዳኘት አይከለከልም በማለት ብቻ አያቆምም:: እነዚህን ጉዳዮች ሥራ ላይ ለማዋል፣ ባለጉዳዮችም ጉዳያቸውን ሥልጣን ላለው አካል ማቅረብ እንዳለባቸው በመገንዘብ፤ በአንቀጽ ፸፰ ንዑስ አንቀጽ ፭ መሠረት የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤትና የክልል ም/ቤቶች የሃይማኖትና የባሕል ፍ/ቤቶችን ሊያቋቁሙ ወይም ዕውቅና ሊሰጡ እንደሚችሉ ደንግጓል:: ሕገ መንግሥቱ ከመጽደቁ በፊት ዕውቅና አግኝተው ሲሠራባቸው ለነበሩ የሃይማኖቶችና የባሕል ፍ/ቤቶች በዚህም ሕገ መንግሥት ዕውቅና አግኝተው እንደሚደራጁ ደንግጓል::

---

[32] John Griffiths, *What is Legal Pluralism?* Journal of Legal Pluralism and Unofficial Law, 1986, pp. 1.

[33] ዝኒ ከማሁ፡፡

[34] Brian Z Tamanaha, *Understanding Legal Pluralism: Past to Present, Local to Global, Sydney Law Review*, Vol 30:375, 2008, pp.3.

ለዚህ አስረጂ የሚሆነን ደግሞ ከ፲፱፻፴፩ ዓ.ም ጀምሮ በሕግ ዕውቅና ተሰጥቷቸው ሲሠሩ የነበሩት የሸሪአ ፍ/ቤቶች በ፲፱፻፺፪ ዓ.ም በይፋ ተደራጅተው እያገለገሉ መሆናቸው ነው፡፡

እንዲህ ዓይነት የሕግ ብዙኀነት /ማለትም የሃይማኖታዊና ባሕላዊ ፍ/ቤቶች በሕግ ማቋቋም/ በሕገ መንግሥቱ የተቀመጠ ስለሆነ መደበኛ የሆነ (Formal) የሕግ ብዙሕነት ሲባል ከዚህ ውጭ ያለ በሕግ ያልታወቀ ነገር ግን የተለያያዩ ጉዳዮችን /ፍትሐ ብሔራዊም ሆነ የወንጀል ጉዳዮችን/ በባሕል የመዳኘት ጉዳይ መደበኛ ያልሆነ (Informal) የሕግ ብዙሕነት ይባላል::[35] የመንፈሳዊ /ሃይማኖታዊ/ ፍ/ቤቶች መቋቋም ሕገ መንግሥቱ እውቅና የሰጠውን መደበኛ የሕግ ብዙኀነት የሚያጠናክር ድርጊት ነው:: ከላይ እንደተብራራውም የመንግሥትና የሃይማኖት መለያየት ከሚለው የሕገ መንግሥቱ መርሕ ጋር የሚጋጭም አይደለም:: ይልቁንም የመንፈሳዊ ፍ/ቤቶች መቋቋም ሕገ መንግሥታዊና ሕገ መንግሥቱ ያለመውን ዓላማ ሊያሳካ የሚችል ነው::

## ፫. የመንፈሳዊ ፍ/ቤቶች አስፈላጊነት

በአንድ ሀገር የሕግ የበላይነትን ለማስጠበቅ መንግሥት የሕግ ተርጓሚ አካላትን (ፍርድ ቤቶችን) ማደራጀት ቀዳሚ ተግባሩ ነው፡፡ እነዚህ መደበኛ ፍርድ ቤቶች መንግሥት የሚያወጣቸውን ሕግጋት የመተርጎም ሙሉ ሥልጣን ያላቸው ሲሆን፤ ማንኛውም ቅሬታ ያለው ሰው ጉዳዩ “በፍርድ ሊወሰን የሚገባው” ከሆነ፤ በእነዚህ መደበኛ ፍርድ ቤቶች የመገልገል ሙሉ መብት አለው፡፡[36] በዚህ ክፍል ለማየት የምንሞክረው ከእነዚህ መደበኛ ፍርድ ቤቶች ሌላ፤ መንፈሳዊ ፍርድ ቤቶች (በተለይም የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ መንፈሳዊ ፍርድ ቤት) መደራጀት ወይም መመሥረት ያለውን ጥቅም ይሆናል፡፡

**፫.፩ የመንግሥትና የሃይማኖት መለያየትን ለማስጠበቅ፣** በኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፲፩ ላይ መንግሥትና ሃይማኖት የተለያዩ ናቸው፤ መንግሥታዊ ሃይማኖት አይኖርም፤ እንዲሁም መንግሥት በሃይማኖት፤ ሃይማኖትም በመንግሥት ጉዳይ ጣልቃ አይገቡም በሚል መደንገጉን ከላይ ጠቅሰናል:: ይህም መንግሥታዊ አስተዳደር ከሃይማኖት ተጽዕኖ የጸዳ (Secular) እንዲሆን ያደርጋል፤ እንዲሁም ሃይማኖታዊ ተ ቋማት ከመንግሥታዊ አስተዳደር ነጻና ራሳቸውን በራሳቸው የማስተዳደር ነጻነት (Institutional Autonomy or Self-determination/Administration) የሰጠ ነው:: የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ የዚህ መብት ተጠቃሚ ስትሆን ተቋማዊ ነጻነቷን በማስከበር ሂደት ግን የሚቀሩ ብዙ ነገሮች አሉ:: ከእነዚህም ጉዳዮች ዋነኛው ራሷን በመቻልና ተቋማዊ ነጻነቷን በማስጠበቅ ሂደት ውስጥ ከመደበኛ ፍ/ቤቶች የሚደርስባት ጫና ነው:: ይህንን ጉዳይ ከማየታችን በፊት የሃይማኖት ተቋማዊ ነጻነት በሌሎች ሀገሮች ዘንድ እንዴት እንደሚታይ በጥቂቱ ለመዳሰስ እንወዳለን::

አብዛኛዎቹ ምሁራን እንደሚሉት መንግሥት በሃይማኖት ጣልቃ ከገባ የሃይማኖቱን ነጻነትና የአማኙን መብት ብቻ ሳይሆን፤ የመንግሥትንም ነጻነትና አሠራር ይጐዳዋል:: ብላክ የተባሉ አሜሪካዊ ምሁር ይህንን ሲገልጹ *«የመንግሥትና የሃይማኖት መቀላቀል መንግሥትን ያዳክማል ሃይማኖትንም ያንቋሽሻል»* ብለዋል (a union of government and religion tends to destroy government and to degrade religion) [37]

---

[35] Alemayehu Fentaw, “Legal Pluralism: Its Promises and Pitfalls for Ethiopia,” Journal of Jimma University Vol. I, No. 1, (2007), pp. 7 & 9.

[36] የኢ/ፌ/ዲ/ሪ ሕገ መንግሥት፤ አንቀጽ ፴፯፣ ፸፰-፹፬፡፡ “ጉዳዩ በፍርድ ሊወሰን የሚገባው” (justiciable matters) የሚለው አገላለጽ ፍ/ቤቶች ሊያዩዋቸው የማይገባና ምንም ዓይነት ዳኝነት ሊጠየቅባቸው የማይገቡ ጉዳዮች መኖራቸውን ያስገነዝበናል፡፡

[37] Justice Black in Engel v. Vitale, 370 (U.S. 1962) pp.421, 431.

ስለሆነም ሁለቱም ተቋማዊ ነጻነታቸውን ይዘው ቢቆዩ ጥቅሙ ለሃይማኖት ብቻ ሳይሆን ለመንግሥትም ጭምር ነው ማለት ነው። በአሜሪካ ለዚህ ጽንሰ ሐሣብ መሠረት የሆነው ሕገመንግሥቱ ሲሆን *"የአሜሪካ ምክር ቤት የሃይማኖትን መቋቋም ወይም ሃይማኖትን በነጻነት የመግለጽ መብትን የሚገድብ ሕግ ማውጣት አይችልም"*፡፡ በማለት ደንግጓል።[38] ይህን አንቀጽ በመንተራስ አሜሪካውያን የራሳቸውን የሕግ ሥርዐት የገነቡ ሲሆን መንግሥትና መንግሥታዊ ተቋማት በሃይማኖትና ሃይማኖታዊ ተቋማት አሠራር ውስጥ ምንም ዓይነት ጣልቃ ገብነት የላቸውም።[39]

ስለሆነም የአሜሪካ ፍ/ቤቶች ሃይማኖት ነክ የሆኑ ክርክሮችን የማየት ሥልጣን የላቸውም። ካዩም የሃይማኖት ነጻነትን ያረጋገጠውን የሕገ መንግሥት አንቀጽ እንደተጻረሩ የሚያስቆጥር ነው። ሃይማኖት ነክ ጉዳዮች (ክርክሮች) ስንል በሂደቱ የሃይማኖቱን ልክ መሆን አለመሆን (truth or falsity of religious belief)፤ የሃይማኖቱን ዶግማ፣ ቀኖና ሥርዐት መተርጎም (interpretation of particular church doctrines)፤ ዶግማው፣ ቀኖናውና ሥርዐቱ ለተባለው ሃይማኖት ያለው ጠቀሜታ (importance of doctrine to the religion) ወዘተ ማለታችን ነው፡፡[40] ይህም መርሕ ከጊዜ ብዛት *"እጅህን ከልክል"* (Hands off) የሚባል ሲሆን መንግሥታዊ ተቋማት (ፍ/ቤቶችን ጨምሮ) ሃይማኖታዊ ጉዳዮችን ከማየትና ከሙተንተን የተከለከሉበት ነው። እነዚህን በመሳሰሉ ጉዳዮች ላይ መደበኛ ፍ/ቤቶች አቅምም ሆነ የሕግ መሠረትና ዕውቀቱ (expert knowledge) እንደሌላቸው ራሳቸው ዳኞቹ የሚመሰክሩት ጉዳይ ነው፡፡ ምክንያቱም "መደበኛ ፍ/ ቤቶች ሃይማኖታዊ ግጭቶችን ለመፍታት ሥልጣን ብቻ ሳይሆን፣ ክህሎቱም የላቸውም" ማለትን መርጠዋልና፡፡[41] እነዚህን በመሳሰሉ ጉዳዮች ዕውቀት፣ የሕግ መሠረትና የማየት ሥልጣን ያላቸው በሃይማኖቱ የተደራጁት መንፈሳዊ ፍ/ቤቶቻቸው ናቸው፡፡

የጀርመን ሕገ መንግሥትና መሠረታዊ ሕጋቸው (Basic Law of Germany) ለሃይማኖት ተቋማዊና ሁለንተናዊ ነጻነት ዕውቅና የሚሰጥ ነው።[42] በዚህም መሠረት መደበኛ ፍ/ቤቶች ሃይማኖታዊ ጉዳዮችን እና የሃይማኖት ተቋማት የሚያስተዳድሯቸውን ተቋማት ለምሳሌ ት/ቤቶች፣ የሕክምና ተቋማት፣ የአረጋውያን መጦሪያ፣ ሕፃናት ማሳደጊያ ወዘተ የሚመለከቱ ጉዳዮችን (ክሶችን) ከማየት ይቆጠባሉ፤ አልያም በጥንቃቄና የሃይማኖቱን ነጻነት በሚያስጠብቅ ሁኔታ ብቻ ያያሉ። አለበለዚያ ግን ሃይማኖቶቹ ባላቸው መንፈሳዊ ፍ/ቤትና ሌሎች ተቋማት እንዲዳኙ ያደርጋሉ።[43] ነገር ግን መንግሥታዊ ፍ/ቤቶች በሌሎች አካላት የሚሰጡት ውሳኔዎች የሰውን እኩልነትና ሌሎች መሠረታዊ ሕግጋትን የሚጻረሩ እንዳይሆኑ ክትትል ያደርጋሉ።

---

[38] *US Constitution, Amendment I:* reads "Congress shall make no law respecting and establishment of religion or prohibiting the free exercise thereof…"

[39] Kyle D. Gobel and Holiman V.Dovers: *An Argument for a more in depth Analysis of Religious Disputes*, (43 Indiana Law Review, 1287, 2010); pp.1292.

[40] Samuelf Levine, *Symposium the Suprene court's hands off approach to religious doctrine: An Introduction*, (Notre Dame Law Review, V.84, No.2; 2009).

[41] Michael G.Weisberg, *Balancing Cultural Integrity Against Individual Liberty: Civil Court Review of Ecclesiastical Judgements,* (25 U.Mich J.L. Ref 955, 1992); pp. 964. "Civil (regular) courts not only lack authority to resolve religious conflics but they are also incompetent to do so".

[42] Art 137 of *German Constitution of 1919,* and Art. 140 of *German Basic Law of 1949.*

[43] Gerhard Robbers, *Church Autonomy in the European Court of Human Rights Recent Development in Germany,* (26 Journal Law and Religion 281, 2010 – 11); pp.287.

ወደኛ ሀገር ጉዳይ ስንመጣ ሕገ መንግሥታችን የሃይማኖት ነጻነትን በተመለከተ መንግሥትና ሃይማኖት የተለያዩ መሆናቸውን ፣ መንግሥት በሃይማኖት ጉዳይ ሃይማኖትም በመንግሥት ጉዳይ ጣልቃ መግባት እንደማይችሉ ተደንግጎ እናገኘዋለን::[44] ነገር ግን የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ የራሷ ተቋማዊ ግልጽነትና ወጥነት ያለው መንፈሳዊ ፍ/ቤት ስለሌላት፤ በቤተክርስቲያኗ አሠራርና ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያላቸው አካላት ወደ መደበኛ ፍ/ቤት ለመሔድ ሲገደዱ፤ ፍ/ቤቶችም ከግንዛቤ ማነስ አልያም የውሣኔውን ውጤት በጥልቀት ካለመመርመር የሕገ መንግሥቱን ድንጋጌ የሚጻረሩ፣ ቤተክርስቲያኗ ተቋማዊ ነጻነት (Institutional Autonomy) የሚጎዳ ውሳኔ ሲሰጡ እናያለን:: ለማሳያነት አሁን በፍ/ቤት እየታየ ያለን አንድ እውነተኛ ክስ በአጭሩ እናንሳ፡፡ አቶ ዘነበ /ለዚህ ጽሑፍ ሲባል ስሙ የተቀየረ/ በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ ቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ መንፈሳዊ ትምህርት ለመከታተል ያመለክታል:: መንፈሳዊ ኮሌጁ ተማሪዎችን የሚቀበልበት የራሱ መስፈርት ያለው ሲሆን፤ ውሳኔውም በዚሁ መሠረት ይሰጣል፡፡አመልካች በታየበት የመንፈሳዊነት፣ አገልግሎትና ሥነ ምግባር ጉድለት ምክንያት በኮሌጁ መንፈሳዊ ትምህርቱን መከታተል እንደማይችል ተገለጸለት:: አቶ ዘነበ ክልከላውን በመቃወም ጉዳዩን ወደ መደበኛ ፍ/ቤት ወሰደው (ስሕተት-፩):: ፍ/ቤቱም ጉዳዩን ተቀብሎ ማስተናገድ ጀመረ (ስሕተት-፪)፤ በዚህ ሳይበቃ ያለ አግባብ ከትምህርት ገበታዬ ታግጃለሁ ብሎ ያቀረበውን ክስ ፍሬ ነገሩን እስኪያይና ውሳኔ እስኪሰጥበት ድረስ አመልካች ትምህርቱን እየተከታተለ እንዲቆይ የሚል ውሳኔ ፍ/ቤቱ ሰጠ (ስሕተት ፫)::

ይህ ነው ሃይማኖታዊ ነጻነት መጋፋት የሚባለው:: መንፈሳዊ ፍ/ቤቱ ቢቋቋም፣ በሁሉም ዘንድ የጠራ ግንዛቤ ቢኖር፣ ለፍ/ቤቱም ግልጽ ሥልጣን ተሰጥቶት ቢሆን ኖሮ ባለጉዳዩ ፍ/ቤት ባልሔደ፡፡ ፍ/ቤቱም እንደዚህ ያለ የቤተክርስቲያንን ሥርዐተ እምነትና አሠራር የሚያናጋ ትእዛዝ ባልሰጠ ነበር:: በሌላም ሁኔታ የቦታ ይገባኛል ክስ የቀረበለት ፍ/ቤት የጸበል አገልግሎት እምነት ከማካሔድ ጋር ብዙም ቀረቤታ ስለሌለው የጸበል ቦታ እንደ ቤተክርስቲያን ይዞታነት አይታይም ብሎ ስለ ጸበል ሃይማኖታዊ ትንታኔ መስጠቱን ታዝበናል:: ሰበር ድረስ በደረሰ በሌላ የክስ መዝገብ ደግሞ፤ ከሰንበቴ ማኅበር ያለአግባብ ታግደናል ያሉ ሦስት የገነተ ጽጌ ቅ/ጊዮርጊስ ማኅበር በኩር ሰንበቴ አባላት ከስድስት ወር ላላነሰ በፍ/ቤት ፍትሕን ሲፈልጉ ነበር፡፡ እንግዲህ ፍ/ቤቶች የሰንበቴ ማኅበሩን ውስጠ ደንብና የአባላቱን ሥነ ምግባር በመተንተን ሂደት ውስጥ ምን ያህል ወደ መንፈሳዊ ጉዳዮች ጠልቀው እንደሚገቡ መገንዘብ ይቻላል::[46]

ስለሆነም በሕገ መንግሥቱ የተቀመጠው የሃይማኖት ነጻነት እንዲከበርና ተቋማዊ ነጻነት እንዲጠበቅ ከተፈለገ መደበኛ ፍ/ቤቶች መንፈሳዊ ጉዳዮችን ከማየትና የቤተክርስቲያኗን ሥርዐትና ቀኖና ከመተንተን ሊቆጠቡ ይገባል:: ቤተክርስቲያኗም አማኞቿ አልያም ሌሎች ግለሰቦች በሰጠችው አስተዳደራዊ ነክ ውሳኔዎች ቅር ከተሰኙ አቤቱታቸውን የሚያሰሙበት የጠራ አሠራርና ተቋም ወጥ በሆነ መንገድ መዘርጋት ይኖርባታል::

---

[44] የኢ/ፌ/ዲ/ሪ ሕገ መንግሥት፤ አንቀጽ ፲፩፡፡

[45] ይህ ክስ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት መናገሻ ምድብ ችሎት እየታየ ያለ ጉዳይ ነው፡፡ የበለጠ ለመረዳት www.dejeselam.org/2011/02/blog-post_10.html.

[46] የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ሰ/መ/ቁጥር ፵፰ሺ፫፻፹፩ የገነተ ጽጌ ቅ/ጊዮርጊስ ማኅበር በኩር ሰንበቴ እና ማሞ ተሰማ፣ ጌታቸው ይልማ፣ ወይንሸት ሙላት፡፡ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት እና ከፍተኛው ፍ/ቤት አባላቱ ለስድስት ወር ከማኅበሩ እንዲታገዱ የተደረገው አላግባብ ነውና ውሳኔው እንዲነሣላቸው ወስነው ነበር፡፡ ነገር ግን ማኅበሩ ጉዳዩን ለሰበር ያቀረበው ሲሆን ጉዳዩ ለሰበር በቀረበበት ወቅት አባላቱ የታገዱበት የስድስት ወር ጊዜ ስለተጠናቀቀ ፍ/ቤቱ ወደ ክርክሩ ከመግባቱ በፊት ለክሱ ምክንያት የሆነው ጉዳይ ስለበቃ መዝገቡን ዘግቶታል፡፡

አለበለዚያ ግን በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፴፯ ሥር የተቀመጠውን ፍትሕ የማግኘት መብት ማጣበብ ይሆናል:: ምናልባት አሁን ያለው ቤተክርስቲያኗ መዋቅር ቅሬታን ለመስማት በቂ ነው የሚል መከራከሪያ የሚነሣ ከሆነ (ምንም እንኳን የጠለቀ ጥናት ቢያሻውም) አሁን ያለው ሥርዐት እኛ ከምንለው በብዙ የተለየ እንደሆነ ለመግለጽ እንወዳለን:: ይህም አንጻራዊ ገለልተኝነት፣ ወጥነት፣ ተደራሽነት፣ ግልጽነት፣ ወዘተ የጎደለው እንደሆነና አሁን ያልናቸውን ዓይነት ቅሬታዎች በሕግ አግባብ ለማየት እጅግ ብዙ የሚቀረው ነው::[47] በተጨማሪም በመደበኛ ፍ/ቤቶች ያሉትን በቁጥር የበዙ ቤተክርስቲያን ቀመስ ክሶች፣ ቤተክርስቲያኗ አሁን የምታያቸው ጉዳዮች ዓይነት፣ በሕግ ፊት ያለው ተቀባይነት እና የውሳኔ ሰጭውን አካል አደረጃጀት ነው፡፡[48]

**፫.፪ የቤተክርስቲያኗን መንፈሳውያን አገልጋይ ሠራተኞች ጉዳይ ለመመልከት፣** ከላይ ካነሣነው ጉዳይ ጋር ተዛማጅ የሆነው ሌላውና ጠቅላይ ፍ/ቤት ግልጽ አቋም የያዘበት ጉዳይ የቤተክርስቲያኗ መንፈሳዊ አገልጋይ ሠራተኞችን የሚመለከት ጉዳይ ነው:: ይህም መደበኛ ፍ/ቤቶች የቤተክርስቲያኗን ነጻነት በማስጠበቅ ሂደት ሊጫወቱ የሚገባቸውን ሚና በግልጽ ያስቀመጠ ነው:: የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በተለያዩ መዝገቦች የቤተክርስቲያኗ መንፈሳዊ አገልጋዮች መንግሥት ባወጣው አሠሪና ሠራተኛ ዐዋጅ ይካተታሉ ወይ? ጉዳያቸውንስ ለማየት መደበኛ ፍ/ቤቶች ሥልጣን አላቸው ወይ? የሚል ጉዳይ ቀርቦለት ነበር::[49] በብዙ ሀገራት የሕግ ሥርዐት እንደታየው የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ይህን ጉዳይ በተደጋጋሚ እያስተናገደ ነው:: እነዚህ አገልጋዮች በቤተክርስቲያኗ በራሷ ሕግና በራሷ ተቋማዊ አደረጃጀት ወጥነት ባለው ሁኔታ የሚታዩ ናቸው:: መደበኛ ፍ/ቤቶችና በሥራ ላይ ያለው የአሠሪና ሠራተኛ ዐዋጅም አይመለከታቸውም በማለት ወስኗል::[50] ይህ ባይሆን ኖሮ መደበኛ ፍ/ቤቶች ካህናት፣ መነኮሳት፣ መርጌቶች፣ ወዘተ. መሥራት ያለባቸውን የሌለባቸውን የሥራ ዓይነት፣ የሥራ ሰዓት፣ መብትና ግዴታቸውን ወዘተ. ሊተነትኑ ይሞክሩ ነበር:: ይህ በብዙ የሕግ ሥርዐቶች እንደ የአገልጋዮች ልዩ ሁኔታ (Ministrial Exception) የሚታይ ሲሆን የመደበኛ ፍ/ቤቶች ድርሻ እጅግ በጣም የተገደበ ነው::

---

[47] ለዚህ ጥናት ሲባል በተደረገ ቃለ መጠይቅ (ከሐምሌ 2003 ኅዳር 2004 ዓ.ም) በምሥራቅ ሐረርጌ ሀገአ ስብከት አገልጋዮች በሐረር ከተማ በሚገኝ አጥቢያ ቤተክርስቲያን እና በሐረማያ ወረዳ ሁለት አብያተ ክርስቲያናት አገልጋዮችና አንዳንድ ምእመናን የሰጡት ግብረ መልስ::

[48] ዝኒ ከማሁ::

[49] የአሠሪና ሠራተኛ ሕግ ዐዋጅ ቁጥር ፫፻፸፯/፲፱፻፺፮፡፡

[50] የፌደራል ጠ/ፍ/ቤት ሰ/መ/ቁጥር ፲፰ሺ.፩፻፲፱/፺፰ በሐመረ ወርቅ ቅ/ማርያም ቤተክርስቲያን ሰበካ ጉባኤ ጽ/ቤት እና እነ ዲያቆን ምሕረት ብርሃኑ ክሶቹ ግን በዚህ ሳያበቁ በተደጋጋሚ ጊዜ እየቀረቡ ተመሳሳይ ውሳኔ እየተሰጠባቸው ይገኛል፡፡ ለምሳሌ የፌደራል ጠ/ፍ/ቤት ሰ/መ/ቁጥር ፴፩ሺ.፩፻፵ መንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤት እና መጋቢ ምስጢር መዝገቡ በላይነህ፣ ፴፰ሺ.፫፻፴፩ የኢ/ኦ/ቤ/ክ በባሌ ሀገረ ስብከት የጎባ ቅ/ገብርኤል ቤ/ክ እና መሪጌታ መርዓዊ ሥዩም በቅርብም በ፵፯ሺ.፰ ኖኅተ ሰማይ ቅ/ማርያም ቤ/ክ እና ዲ/ን አያሌው አዲሱን መመልከት ይቻላል። ውሳኔው ቤተክርስቲያኗ ውስጥ በመደበኛ መንፈሳዊ አገልግሎት የሚሳተፉ ሠራተኞች በአሠሪና ሠራተኛ ዐዋጅ ቁጥር ፫፻፸፯/፲፱፻፺፮ አይተዳደሩም፣ መደበኛ ፍ/ቤቶችም ይህንን መሰል ክርክር ለማየት ሥልጣን የላቸውም ብሎ ወስኗል፡፡ እነዚህንም ክርክሮች ቤተክርስቲያኗ ባላት ግጭት መፍቻ ዘዴ መፍታት እንደሚገባትና እንደምትችልም አስቀምጧል፡፡ ነገር ግን ሌሎች ከመንፈሳዊ አገልግሎት ጋር ቁርኝት የሌላቸው ሠራተኞች (ለምሳሌ ሒሳብ፣ ንብረት ክፍል፣ ስታትስቲክስ ሠራተኞች) በዐዋጁ እንደሚካተቱና ክሳቸውም በመደበኛው ፍ/ ቤት መሰማት እንደሚችል ወስኗል፡፡ ይህንን ውሳኔ ከዐዋጅ ቁ. ፬፻፶፬/፲፱፻፺፯ ጋር አብረን ስንረዳው ውሳኔውን ሁሉም በሀገሪቱ የሚገኙ ፍ/ቤቶች ሊከተሉት እንደሚገባና ራሱ ሰበር ሰሚው በሌላ ጊዜ ካልቀየረው በቀር እንደ ሕግ እንደሚያገለግል እንገነዘባለን፡፡

እነዚህ አገልጋዮች አሁን ባለው የሕግ ትርጓሜና ውሳኔ መሠረት ጉዳያቸውን ወደ መደበኛ ፍ/ቤት ይዘው መሔድ አይችሉም፤ ቢሔዱም ፍ/ቤቱ የማየት ሥልጣን አይኖረውም፡፡ ምክንያቱም የፌ/ጠ/ፍ/ቤት በሰበር ችሎት ተመልክቶ የሰጠው የሕግ ትርጓሜ የሕግ ያህል ገዢ ስለሆነና በሀገሪቱ የሚገኙ ሁሉም ተቋማት ውሳኔውን ወይም ትርጓሜውን እንዲከተሉት ስለሚያስገድድ ነው፡፡[51] ቤተክርስቲያኗ ይህንን ዕድል ተጠቅማ የራሷን መንፈሳዊ ፍ/ቤት ማቋቋም ካልቻለች፣ ተመሳሳይ የሆኑና ለቁጥር የሚያታክቱ ቅሬታዎችን በራሷ ተቋም ሥር ካልፈታችና ውሳኔ ካልሰጠች ወደፊት የጠቅላይ ፍ/ቤቱ ውሳኔ ቢቀየር የሚደርሰው ከፍተኛ ጉዳት ይሆናል፡፡ ጠለቅ ያለ ምርምር የሚያሻው ቢሆንም አገልጋዮች ወደ መደበኛ ፍ/ቤት የሚሔዱት የቤተክርስቲያኗ መዋቅር እነዚህን ጉዳዮች በበቂ፣ በቀልጣፋና ገለልተኛ በሆነ መንገድ ለመፍታት ስላልቻሉ ይመስላል፡፡ የመንፈሳዊው ፍ/ቤት መቋቋም ግን የቤተክርስቲያኗ አገልጋዮቿ ወደ ፍ/ቤት በመጓተት የሚያጠፉትን ጊዜ፤ ዕውቀትና ሀብት ከመቆጠቡም በላይ በአገልጋዮችና ቤተክርስቲያኗ መካከል ያለውን መንፈሳዊና ምስጢራዊ ግንኙነት ለመጠበቅና ለማጐልበት ያስችላል፡፡

ፍትሕ ርትዕት የሆነች ቤ/ክ፣ የራሷ የበለጸገ ሕግ ያላት ቤ/ክ ፣ ለመደበኛ የመንግሥት ሥርዐትና ተቋማት አደረጃጀት መሠረት የሆነች ቤ/ክ፣ መሪ በሆነችበት ሕግን የማስከበርና ሰውን በርትዕ የመዳኘት ጉዳይ ኋላቀርና ተወቃሽ መሆን የለባትም፡፡ አገልጋዮቿም የቤተክርስቲያኗ ዕንቁ ሀብቶች በመሆናቸው መብትና ጥቅማቸው የሚጠበቅበትን የውስጥ አሠራር እና ቅሬታቸውን በግልጽና በሕግ አግባብ የምትፈታበትን የመንፈሳዊ ፍ/ቤት መዋቅር ማደራጀት ይኖርባታል፡፡ ይህም ይሆን ዘንድ መንግሥትን መጠየቅና ተጽእኖ መፍጠር ይኖርባታል፡፡

**፫.፫ በሕገ መንግሥቱ የተሰጡ መብቶችን ለማስፈጸም፣** ከላይ በክፍል ሁለት ሥር የኢ.ፌዴሪ ሕገ መንግሥት የሕግ ብዙኅነትን እንዴት እንዳካተተ ተመልክተናል፡፡ በዚህም ሃይማኖታዊና ባሕላዊ ሕጎች፤ በሕግ ሥርዐቱ ውስጥ ቦታ እንደተሰጣቸው እንዲሁም ሃይማኖታዊና ባሕላዊ ፍ/ቤቶችም ሊቋቋሙ መቻላቸውን ተገንዝበናል፡፡ ለዚህም ሕግ አውጪው የመንግሥት አካል አስፈላጊውን ሁኔታ ማመቻቸት ይኖርበታል፡፡ ይህም ሕገ መንግሥቱ በሚያዘው መሠረት ፍ/ቤቱን ማቋቋም ወይም ዕውቅና መስጠትና የመሳሰሉትን ያካትታል፡፡ ይህ የመንግሥት አካል ይህንን ሳያደርግ በመቅረቱ ግን ዜጐች በሕገ መንግሥቱ የተሰጣቸውን መብት መጠቀም ሳይችሉ እየቀሩ ነው፤ የመጠቀም መብታቸውም እየተጣበበባቸው ነው፡፡ ይህም የመንግሥት አካላት በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፴፬/፭/ እና ፸፰/፭/ መሠረት የተሰጣቸውን የሕገ መንግሥቱን ድንጋጌዎች የማክበር፣ የማስከበርና የማስፈጸም ድርሻ በሚፈለገው መጠን እየተወጡት አይደለም ለማለት ያስደፍራል፡፡

ከላይ የተብራራው የሕግ ብዙኅነት ወይም የሃይማኖት ሕገ ብዙኅነት (Religious Legal Pluralism) መርሕ ሁሉንም ሃይማኖቶች ለማክበርና ለማስከበርና ለሀገር ሁለንተናዊ ሰላም አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ ከሚደረግበት መንገድ ዋነኛው ነው፡፡ በፌዴራሊዝም ሕገ ብዙሕነት ላይ ከፍተኛ ጥናትና ምርምር ያደረገው ጉድማን “Religious legal pluralism is an appropriate description for these legal regimes that admit multiple hybrids, and sometimes overlapping and conflicting bodies and systems of law”. *“ሃይማኖታዊ ሕገ ብዙሕነት ብዙ ቅይጥ አንዳንዴም የሚወራረሱና የሚቃረኑ ተቋማትና ሕጐች መኖራቸውን ለሚቀበል የሕግ ሥርዐት ትክክለኛው መገለጫው/መግለጫው/ ነው”[52] (ትርጉም የአዘጋጆቹ)* ብሏል፡፡

[51] የፌደራል ፍ/ቤቶች ዐዋጅን እንደገና ለማሻሻል የወጣው ዐዋጅ ቁ. ፬፻፶፬/፲፱፻፺፯ አንቀጽ ፪። ነገር ግን ሰበሩ ይህንን ቀድሞ የወሰነውን ውሳኔ በሌላ ጊዜ ሊቀይረው እንደሚችል በተመሳሳይ መልኩ ተቀምጦ ይገኛል፡፡

[52] Josh Goodman, *Divine Judgement Judical Review of Religious legal system in India and Israel,* (32 Hasting jut & Comparative Law Review, 477, 2009), pp. 478.

ለዚህም የብዙ ሀገሮችን የሕግ ሥርዐት እንደማሳያ መጠቀም ይቻላል፡፡ ለምሳሌ ሕንድ እና እስራኤል በዲሞክራሲ ላይ የተገነባ መንግሥታዊ የሕግ ሥርዐት ሲኖራቸው የሃይማኖት ሕጐች በተወሰኑ የግልና ቤተሰባዊ ጉዳዮች ላይ ሙሉ ተፈጻሚነት አላቸው፡፡[53] የግል ጉዳዮችን የሚገዛ ሕግ (personal law) ስንል የቤተሰብ ሕግ፣ ውርስ፣ ፍቺ፣ ንብረት ክፍፍል፣ የልጆች አሰተዳደግ፣ ቀለብ መስጠትና ሌሎች የግል ሁኔታዎችን የሚደነግግ ማለታችን ነው፡፡[54] ለምሳሌ በእሥራኤል ሃይማኖታዊ ፍ/ቤቶች ይህንን በመሳሰሉ ጉዳዮች ሙሉ ሥልጣን ሲኖራቸው ፣ በሕንድ እንደተከራካሪዎቹ ሃይማኖት መደበኛ ፍ/ቤቶች ጭምር የሚጠቀሟቸው ሕጐች ይለያያሉ፡፡ ይህም ማለት የሒንዱ እምነት ተከታዮች ለፍቺ ጉዳይ ፍ/ቤት ቢቀርቡ ሒንዱ ቀመስ ሕግ ተፈጻሚ ይሆናል ማለት ነው፡፡[55] በደቡብ አፍሪካም ፍ/ቤቶች ባሕላዊ የሆኑ የጐሣውን ሕግ (tribal group) ተፈጻሚ እንዲያደርጉ ሕገ መንግሥቱ ያዛል፡፡[56] ይህም ሃይማኖታዊ ሕገ ብዙኀነት የግለሰብን ማኅበረሰብንና አናሳ (minority) መብትን ለማስጠበቅ ዐይነተኛ መንገድ መሆኑን ያሳየናል፡፡ ለምሳሌ በእስራኤል የሚኖሩ ሙስሊሞች በራሳቸው ሃይማኖታዊ ሕግ እንዲዳኙ ባይፈቀድ ኖሮ አናሳ በመሆናቸው የእነሱን እሴት፣ ባሕልና አኗኗር የሚያንጸባርቅ የቤተሰብ ሕግ በመንግሥት እንደማይወጣ ይታወቃል፡፡

የእኛ ሀገር የሕግ ሥርዐት በሕገ ብዙኀነትና አሐዳዊነት ተወጥሮ እናገኘዋለን፡፡ ተቋማት፣ ዜጐች ቤተሰባዊና ግላዊ ጉዳያቸውን በመረጡት ሕግና በሃይማኖታቸው መሠረት እንዲፈቱ ከማድረግ ይልቅ ወጥነት ያለው አስገዳጅ ሕግ ለማውጣትና ለማስፈጸም ይሞክራል፡፡ የፌደራልና የክልሎች የቤተሰብ ሕግ ሲረቀቅ፣ እንዲሁም የወንጀል ሕጉ ሲሻሻል የነበሩት አለመግባባቶች ለዚህ ማሳያ ናቸው፡፡ ለምሳሌ የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ ጋብቻን እስከ ሰባት ቤት ትከለክላለች፤ በጋብቻ ላይ ጋብቻን አትፈቅድም፤ አማኞችም እንዳይፈጽሙት አጥብቃ ታስተምራለች፡፡ ሌሎች የሃይማኖት ድርጅቶች በተለይ እስልምና እምነት ተከታዮች ግን ከዚህ የተለየ ሕግ አላቸው፡፡ ይህንን ሁለት ተቃርኖ ለማጣጣም ሲባል ብቻ የወጡት ሕጐች የሁሉንም ሃይማኖቶች ፣ እሴቶችና ባሕሎች ያላገናዘበ ነው፡፡[57] ይህ በመሆን ፈንታ ግን እያንዳንዱ ሃይማኖት ያለውን የራሱን የቤተሰብ ሕግ እንዲተገብር ቢፈቀድ፣ ተቋማዊ አደረጃጀት ቢመቻችና ዜጐች አማራጭ ቢኖራቸው ግላዊና ሃይማኖታዊ እሴቶቻቸውን በሚያስከብርና በሚያንጸባርቅ ሕግ በተዳኙ ነበር፡፡

በሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ስናየው ሕገ መንግሥት አልፎም የቤተሰብ ሕጉ የሰጠው ጥቂት ቦታ ቢኖርም የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ ያላትን ሕግ፣ እሴትና ባሕል በአማኞቿ ዘንድ ለማስፈጸም እየተቸገረች ትገኛለች፡፡ ለምሳሌ ፍትሐ ነገሥቱ የቤተሰብና የግል ጉዳዮችን በተመለከቱ ምሉዕ ሊባል በሚችል መንገድ መሠረታዊ ሕግጋትን ያስቀመጠ ሲሆን ተርጓሚና አስፈጻሚ በማጣቱ ብቻ ሲተገበር አናየውም፡፡[58] ቤተክርስቲያኗ የራሷ ሕግ እንዳላት ሁሉ ፍ/ቤትም ቢኖራት ኖሮ ዜጐች በመረጡት ተቋምና በፈቀዱት ሕግ ሊዳኙ በተቻላቸው ነበር፡፡

---

[53] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 483፡፡

[54] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 479፡፡

[55] በሌሎች የአፍሪካ ሀገራት ለምሳሌ ናይጄሪያ፣ ደቡብ ሱዳን ወዘተ ተመሳሳይ ሕጐች እንዳሉ ልብ ይሏል፡፡ See Tiernan Mennan, *Legal Pluralism in Southern Sudan, Can the Rest of Africa show the way*? Afr. Pol'y J, 2007.

[56] Goodman, Supra note 52, p. 483; *South African Constitution of 1996*, Section 211.

[57] ይኸውም ለምሳሌ የፌዴራሉ የቤተሰብ ሕግ ጋብቻን እስከ አክስትና አጎት ብቻ የከለከለ ሲሆን ከዛ በኋላ ግን መጋባት ተፈቅዷል፡፡ የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ፣ ዐዋጅ ቁ. ፪፻፲፫/፲፱፻፺፪፣ አንቀጽ ፰፡፡

[58] ፍትሐ ነገሥት፣ አንቀጽ ፳፬።

በሌላም በኩል ፍ/ቤቶች ተፈጻሚ የሚያደርጓቸውን ሕጐች እንደተከራካሪዎቹ ፍላጐት፣ ምርጫና ሃይማኖት ለመቀያየር የሚያስችል አሠራር የለንም:: በመሆኑም ሕገ መንግሥቱ ፈቅዶ ሳለ አንድ ወጥ በሆነና የተከራካሪዎችን ሃይማኖታዊ አቋምና እሴት የማያንጸባርቁ ሕጐችን ተፈጻሚ ለማድረግ ሲሞከር እናያለን:: ስለሆነም ቤተክርስቲያኗ በሕገ መንግሥቱ የተሰጣትን መብት ተጠቅማ አማኞቿ ሲፈቅዱና ሲፈልጉ ብቻ በሃይማኖታዊ ሕግ እንዲዳኙ ለማድረግ የራሷን ፍ/ቤት ማቋቋም ለዚህም አጥብቃ መሥራት ይገባታል:: መንግሥትም በተለይ ሕግ አውጪው ይህንን ማድረግና ማገዝ ሕገ መንግሥቱን መተግበርና የዜጎችን መብት ማስከበር የተቋቋመለትም መሠረታዊ ዓላማ መሆኑን መገንዘብ አለበት፡፡

**፫.፬ ፈጣንና ጥራት ያለው ውሳኔ በአነስተኛ ወጪ በልዩ ፍ/ቤቶች ማግኘት፣** ሌላው መንፈሳዊ ፍ/ቤት ቢቋቋም ለሀገርና ለመንግሥት የሚሰጠው ጥቅም መደበኛ ፍ/ቤቶች ሁሉንም ጉዳይ በተወሰነ ባለሙያ ብቻ እንዲያዩ የሚደረግበትን ሥርዐት ማስቀረት ነው:: ይህም የልዩ ፍ/ቤቶች (Specialized Courts) መቋቋም ጥራት ያለው ፍትሕ በባለሙያዎች እንዲወሰን (expert dispute resolution) ከማድረጉም በላይ ሃይማኖታዊና ባሕላዊ እሴቶችን ለመጠበቅና መደበኛ ፍ/ቤቶችን የጠለቀ ዕውቀት በሌላቸው ጉዳዮች እንዳይቸገሩ ያደርጋል::[59] በተለይ በዝርዝር (technical) ጉዳዮች (ለምሳሌ ሃይማኖታዊ) ላይ ፍ/ቤቶች ባለሞያን እየጠሩ ለማስተንተን ከመሞከር ይልቅ እንደነገሩ ሁኔታ ባለሞያ የሆኑ ዳኞች (Judicial expertise) ማፍራት ተመራጭ ይሆናል::[60] ስለሆነም እንደ መንፈሳዊ ፍ/ቤት ያሉ ልዩ ፍ/ቤቶች ቢበራከቱ መደበኛ ፍ/ቤቶችን በማገዝ የበለጠ ታማኝ፣ ጥራት ያለው፣ ሁሉንም ሁኔታዎች ያገናዘበና ያጣጣመ ውሳኔ እናገኛለን::

ከዚህም በተጨማሪ የመንፈሳዊ ፍ/ቤቱ መቋቋም መደበኛ ፍ/ቤቶች ላይ ያለውን የሥራ ጫና እንደሚቀንሰው ይገመታል:: በተገልጋዮች ወገን ስናየው ደግሞ ግለሰባዊና የቤተ ሰብ ጉዳዮች በመንፈሳዊ ፍ/ቤት እንዲታዩ ዕድሉ ቢሰፋ የገንዘብ፣ የጊዜና የባለሞያ ብክነትን በአያሌው ይቀንሳል::[61] ደፋና ሃከር የተባሉ ባለሞያ በእስራኤል መንፈሳዊ ፍ/ቤቶች (Rabbinical courts) ላይ ያደረጉት ጥናት ለዚህ ትልቅ ምሳሌ ነው፡፡ ጥናቱ መደበኛ ፍ/ቤቶችንና መንፈሳዊ ፍ/ቤቶችን የሚያነጻጽር ሲሆን በወጪ፣ በጊዜ፣ በቅልጥፍና፣ በእርካታና በተአማኝነት ላይ ያጠነጠነ ነበር:: ውጤቱም መንፈሳዊ ፍ/ቤቶች በአነስተኛ ወጪ የተሻለና ፈጣን ፍትሕን ለተጠቃሚዎች እያስገኙ እንደሆነ ያጠቃልላል::[62] በተጨማሪም መንፈሳዊ ፍ/ቤቶቹ ለተገልጋዮች የሚያሳዩት አቀራረብ የተንዛዛና የተወሳሰቡ የሕግ ሥነ ሥርዐቶችን /ለምሳሌ የሕግ ባለሞያ ብቻ የሚያውቀውና የሚጠቀምበት የማመልከቻ አቀራረብና የክርክር ሥርዐት/ በማቅለል ያለ ጠበቃ እንዲከራከሩ ዕድልን ፈጥረዋል፡፡[63] እንዲያውም በየትኛውም ጉዳይ ከጠበቆች በላይ ዋነኞቹ ባለጉዳዮች ሐሳባቸውን በፍ/ቤቱ እንዲያንጸባርቁ በማድረግ የጠበቃ ወጪን አስቀርተዋል::

[59] ይህ ማለት መደበኛ ዳኞች ባለሞያ አይደሉም ለማለት ሳይሆን መደበኛ ዳኞች በሁሉም የሕግና ማኅበራዊ ጉዳዮች ላይ በቂና የጠለቀ ዕውቀት ላይኖራቸው ይችላል ለማለት ነው:: ለምሳሌ አንድ በፍትሐ ብሔር ችሎት የሚሠራ ዳኛ በቤተሰብ፣ ውርስ፣ የንብረት ክርክር ወዘተ ላይ ሙሉና እኩል የጠለቀ ዕውቀት ላይኖረው ይችላል:: ነገር ግን የተለየ ፍ/ቤት ለምሳሌ መንፈሳዊ ፍ/ቤት፣ የሠራተኛና አሠሪ ቦርድ ወዘተ የሚሠራ ዳኛ በዚያ ሕግ ዙሪያ የጠለቀ ዕውቀት ልምድና ግንዛቤ ይኖረዋል:: Charles H.Koch, Jr., *The Advantages of the Civil Law Judical Design as the Model for Emerging Legal System,* 413760, p.11; available at http://ssrn.com/abstract:

[60] ዝኒ ከማሁ፡፡

[61] Daphna Hacker, *Religious Tribunals in Democratic States: Lessons from the Israeli Rabbinical Courts*, (2008 available at http//ssrn.com/abstract169/, 671); pp. 34.

[62] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 10፡፡

[63] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 12፡፡

ተከራካሪዎችም በፍትሕ ሥርዐቱ ቀጥተኛ ተጠቃሚና ተዋናይ እንዲሆኑ አድርገዋል፤ በእርቅ የመጨረስ ዕድልን አስፍተዋል፤ የውሳኔውን ተአማኝነት አሳድገዋል::[64] እንደውም ብዙ ጊዜ ራሳቸው የማመልከቻ ቅጽ (Form) አዘጋጅተው በመጠበቅ ተከራካሪዎች መሠረታዊ መረጃዎችን ብቻ በመሙላት በቀላሉ ፍትሕ እንዲያገኙ አግዘዋል፡፡ በተጨማሪም መንፈሳዊ ፍ/ቤቶቹ ራሳቸውን ለማስተዋወቅ በሚያደርጉት ጥረት ተመራጭ ሆነዋል ፤ ዜጐች ጉዳያቸውን ወደ መንፈሳዊ ፍ/ቤት ይዘው እንዲቀርቡ አበረታተዋል:: በዚህም የፍትሕን ተደራሽነት (Access to Justice) ለማሳካት እገዛ አድርገዋል::[65]

ወደኛ ሀገር ተጨባጭ ሁኔታ ስናመጣው የመንፈሳዊ ፍ/ቤት እንደ ልዩ ፍ/ቤት (Specialized Court) ቢቋቋም የተቀላጠፈና ጥራት ያለው ፍትሕ በብቁ ባለሞያዎችና በጥቂት የገንዘብ ወጪ ማስገኘት ይቻላል:: ዜጐችም ፍትሕ የማግኘት መብታቸውን በአማራጭነት ወደዚሁ ፍ/ቤት በማቅረብ ሊጠቀሙበት ይችላሉ:: ከዚህም የሚሰጠው ውሳኔ ባሕላቸውን፣ ሃይማኖታቸውንና ሌሎች እሴቶቻቸውን የሚያስጠብቅ ይሆናል:: ቤተክርስቲያኗ የራሷ ሕግና ሊቃውንት እንዲሁም እስከ ግለሰቦች ደጅ የሚደርስ በማእከል የሚመራ ኢ-ማእከላዊ (Decentralized) የሆነ መዋቅር ስላላት፤ መንፈሳዊ ፍ/ቤቱ ቢቋቋም የሁሉንም ፍላጐት ባለሞያን በመጠቀምና በቅርበት ለማሟላት ያስችላታል::

**፫.፭ የቤተሰብና ግለሰባዊ ሰላምን ለማጠናከር** ፣ ከዚሁ ጋር የሚቀራረበው ሌላው የመንፈሳዊ ፍ/ቤት ጥቅም ሳይንሳዊ ቀመርን በመጠቀም ግጭትን ከተቻለ ለመከላከልና ለማስወገድ፤ ካልተቻለ ደግሞ የተለያዩ ዘዴዎችን በየደረጃው በመጠቀም ለመፍታት ማገዝ ነው::[66] ጠብና ክርክሮችን በመከላከሉ ረገድ እስካሁን ታደርግ እንደነበረው ሁሉ ቤተክርስቲያኗ በተለይ ቤተሰቦች በሰላምና በመተሳሰብ እንዴት መኖር እንዳለባቸው በማስተማር እንድትገፋበት የሚያደረግ አቅም ይፈጥርላታል፡፡ መንፈሳዊ ፍ/ቤቱ ቢቋቋም ደግሞ ይህንን ድርሻዋን የበለጠ ተቋማዊ በሆነ መንገድ ለማከናወን፣ ተሳትፎዋን ለማስፋፋትና የቤተሰብን ሠላም ለማጠናከር ይረዳታል፡፡ ይህም በሕገ መንግሥቱ ለቤተሰብ የተሰጠውን ጥበቃ የበለጠ ለመጠበቅና ለመተግበር ያግዛታል፡

ግጭቱም ቢከሰት ቤተክርስቲያኗ መንፈሳዊ ፍ/ቤቷን ተጠቅማ ፈጥና በመድረስና ሳይንሳዊ በሆነው የግጭት መፍቻ ዘዴዎች ለመጠቀም የተሻለ አቅም ይኖራታል፡፡ ይህም ከተቻለ በንግግር (Negotiation)፤ አለበለዚያም በሽምግልና (Conciliation) ካልሆነ ደግሞ በክርክር (Litigation) ለመፍታት ያስችላታል፡፡ ቤተሰብ ከፍተኛ የሕግ ጥበቃ የሚገባው/የተደረገለትም/ ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚያሻው (sensitive and fragile) ተቋም ስለሆነ ክርክር የመጨረሻው እንጂ ብቸኛው የግጭት መፍቻ ዘዴ አይደለም፡፡[67] መደበኛ ፍ/ቤቶችም በፍትሐ ብሔር ሕግ አንቀጽ ፫ሺ.፫፻፯-፫ሺ.፫፻፵፮፣ ፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዐት ሕግ አንቀጽ ፪፻፸፬-፪፻፸፱፣ የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ ፩፻፲፰ እና የመሳሰሉት እና በሌሎችም ሕጎች መሠረት ለማስታረቅ መሞከር እንዳለባቸው የተወሰነ ቢሆንም የፍ/ቤቶች ተቋማዊ አደረጃጀት፣ አሠራር፣ የክስ መብዛትና ነገሩ እየከረረ የሚሔድ በመሆኑ ጉዳይን በእርቅ ለማስጨረስ በአያሌው ሲቸገሩ እናያለን፡፡

[64] ዝኒ ከማሁ፡፡
[65] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 14፡፡
[66] Isaac Diianni, *The Role of Competition in the Market for Adjudication*, (18 Sup. Ct. Econ. Rev. 203, 2010); pp. 2000.
[67] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 206፡፡

መንፈሳዊ ፍ/ቤት ቢቋቋም ግን አሁንም እየሠራች ያለውን የማስታረቅና የማስማማት ሥራ ቤ/ኗ በተጠናከረ እና ተቋማዊ በሆነ መንገድ ሕጋዊ ውጤቱን ሳያጣ ለመከወን ያስችላታል፡፡ ይኸውም ተከራሪዎቹ ጉዳያቸውን በራሳቸው እንዲፈቱ ምክርና አቅጣጫ በመስጠት፣ ካልሆነም ሽማግሌዎች እንዲመረጡ አድርጋ (በሕጉ አግባብነት) እንዲሸማገሉ (conciliate) በማድረግ፣ ያም ካልሆነ ደግሞ መንፈሳዊ ፍ/ቤቱ ውሳኔውን እንዲያስተላልፍ በማድረግ ማለት ነው፡፡ በዚህ ሁሉ ሂደት ቤተክርስቲያኗ ነገሩን በቅርበት በመከታተል፣ በፍጥነትና በጥራት፣ ቤተክርስቲያኗ እና ገዥ በሆኑ የሀገሪቷ ሕግጋት መሠረት እልባት እንዲያገኝ ማድረግ ያስችላታል፡፡ በመሆኑም መንግሥትና መደበኛ ፍ/ቤቶች ከሥራ ጫና እና በቤተሰብ መበታተን ምክንያት ከሚመጣ ቀውስ ይድናሉ፡፡ ተከራካሪ ወገኖችም የሚፈልጉትን ውጤት ታማኝ በሆነ መንገድና በመረጡት የፍትሕ አካል ያገኛሉ፤ ቤተክርስቲያኗም ያለባትን መንፈሳዊና ማኅበራዊ ሓላፊነት በተደራጀና ተቋማዊ በሆነ መንገድ ለመወጣት ያስችላታል፡፡

**፫.፮. በሕግ ዕውቅና ያልተሰጣቸውን እሴቶች /Extra-Legal Relation/ ለመጠበቅ፣** በተጨማሪም በሕግ ጥበቃ ያልተሰጣቸው፤ ነገር ግን እጅግ ብዙ የሰውንና ማኅበረሰብን ማንነትና እሴቶች የሚገልጹ ለሃይማኖቱም ምልክትና ገላጭ ባሕል የሆኑ ሁኔታዎች አሉ፡፡ እነዚህም በማኅበራዊ ግንኙነቱ በኩል ወሳኝ የሆኑ በሕጋችን ግን ያልተካተቱ (extra-legal) ጉዳዮች ናቸው፡፡ ምንም እንኳን ማኅበረሰቡ መገለጫውና የሚጠብቀው እሴት ቢሆንም መደበኛው ፍ/ቤቶች ለዚህ ተቋም ጥበቃ ለመስጠት ይቸገራሉ፡፡ ቢጥሰው የማኅበረሰቡን ሠላምና አብሮ መኖር የሚያናጋ ሲሆን በሰዎች መካከል ቅራኔን በመፍጠር ወዳልተፈለገ አቅጣጫ የሚመራ ነው፡፡ ለምሳሌ የክርስትና ልጅና አባት ግንኙነት በባሕልና በቤተክርስቲያኗ ሕግ (ፍትሐ ነገሥት) ሕጋዊ ግንኙነት ስለሆነ በፍትሐ ነገሥቱ እንደ ቅርብ ዝምድና ተቆጥሮ የጋብቻ መከልከያ አንድ ነጥብ ነው፡፡[68] በመደበኛ ሕግ ግን ጥበቃ አልተደረገለትም፡፡ መተጫጨትም በፌዴራሉ የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ ምንም ጥበቃ ያልተሰጠው ቤተክርስቲያኗ እና በአብዛኛቹ የእምነቱ ተከታዮች ዘንድ ግን እየጠበቀው ያለው የማንነት መገለጫ የሆነ ግንኙነት/እሴት ነው፡፡ የመንፈሳዊው ፍ/ቤት መቋቋም ግን ለክርስትና ልጅ እና መተጫጨት የመሳሰሉ በሕግ ጥበቃ ያልተደረገላቸውን እሴቶች (extra-legal relations) ጥበቃና እውቅና በመስጠት የማኅበረሰቡን ግንኙነት ጤናማና ሠላማዊ ለማድረግ ያግዛል፡፡

ስለሆነም የመንፈሳዊ ፍ/ቤቱ መቋቋም ሁለንተናዊ ጥቅም የሚሰጠው ለቤተክርስቲያኗ ብቻ ሳይሆን ለመንግሥት፣ ለዜጎች እና ለተቋማት ጭምር ነውና ሁሉም ተረባርቦ እውን ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

## ፬ ሃይማኖታዊ ፍርድ ቤቶች በሌሎች ሀገራት

ይህ ክፍል በዋናነት የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖታዊ ፍ/ቤት በእኛ ሀገር መቋቋሙ ልዩና ያልተለመደ እንዳልሆነና ሃይማኖታዊ ፍ/ቤቶች በሌሎች ሀገራትም የሕግ ዕውቅና አግኝተው እንደተቋቋሙ ግንዛቤ ያስጨብጣል፤ ስላደረጃጀታቸውና አሠራራቸውም ጥቂት ልምድ ለመውሰድ ያግዘናል፡፡ ለዚህ ይረዳ ዘንድም የአሜሪካን፣ የሩስያን፣ የእስራኤልንና በኢትዮጵያ የሚገኙ የሸሪአ ፍ/ቤቶችን ልምድና የሥራ እንቅስቃሴ እንዲሁም ለተከታዮቻቸው እየሰጡ ያሉትን ጥቅም ይዳስሳል፡፡[69]

---

[68] ፍትሐ ነገሥት፣ አንቀጽ ፳፬፣ ቁጥር ፰፻፳፱፡፡

[69] በዚህ ርእስ ሥር ከብዙ ሀገራትን ልምድ ለመቅሰም እንዲያስችል ሆኖ የጥቂቶቹ ብቻ ተዳሷል፡፡ ከኢትዮጵያ ኦ/ተ/ቤ/ክ ጋር ተቀራራቢ ዶግማ ካላቸው ሀገራት ልምድ ለመቅሰም ቢሞከርም የሚገኘው ልምድ እንደሚታሰበው ምሉዕ አለመሆኑ፣ የተደራጀ መረጃ ለማግኘት ከባድ መሆኑ፣ አንዳንዶቹም (ለምሳሌ ግብጽ) የተገለጸው ፍ/ቤት ስለሌላቸው በብዙ አልተሔደበትም፡፡ ይልቁንም ጥሩ ልምድ ሊገኝ የሚችልባቸውን ሀገራት ብንከተላቸው ከሀገራችን ሕግ ሥርዐት ጋር በቀላሉ የሚሰናሰሉትን መርጠናል፡፡

**፬.፩ የሩሲያ ልምድ** በሩሲያ ሃይማኖታዊ ፍርድ ቤቶች በሕጋዊነት የተቋቋሙ ሲሆን የሩሲያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያንም የራሷን ፍ/ቤት መሥርታለች::[70] እነዚህ ሃይማኖታዊ ፍ/ቤቶች በቤተክርስቲያን የውስጥ ጉዳዮችና መንፈሳዊ ሥራዎች ላይ ሥልጣን ያላቸው ሲሆን ሃይማኖታዊ የሆኑ የሕግ ሥነ ሥርዐቶችን ይከተላሉ::[71] የፍ/ቤቶቹ አሠራርና አወቃቀር የተቃኘው በቤተክርስቲያኗ ቅዱስ ሕጐች፣ ደንቦችና በራሷ የፍ/ቤቱ ደንቦች ናቸው::[72] የሩሲያ ኦርቶዶክስ ሃይማኖታዊ ፍ/ቤት አወቃቀር ሦስት ደረጃዎች ሲኖሩት እንደሚከተለው ተመልክተነዋል፡፡

**ሀ/ የአጥቢያ ቤተክርስቲያን ፍርድ ቤት (The Diocesan Court)** ይህ ፍ/ቤት በሩሲያ ቤተክርስቲያን የመጀመሪያ ደረጃ ሃይማኖታዊ ፍ/ቤት ሲሆን በእያንዳንዱ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን በሚነሡ ጉዳዮች ላይ የመዳኘት ሥልጣን ተሰጥቶታል:::[73]

የዚህ ፍ/ቤት ዳኛ ለመሆን የክህነት ማዕረግ አስፈላጊ ሲሆን በተጨማሪም የቤተ ክርስቲያኑ አስተዳዳሪ በሆኑት ጳጳስ ይሁንታን ሊያገኝ ይገባል:: ነገር ግን የዚህ ፍ/ቤት አባላት ከሆኑት ውስጥ ቢያንስ ሁለቱ በቤተክርስቲያኗ ጳጳስ አቅራቢነት በቤተክርስቲያኗ ምልአተ ጉባኤ ሊመረጡ ይገባል:: ጳጳሱ ከዳኞቹ በተጨማሪ ሦስት ዓመት የሥራ ዘመን ያለውን የፍ/ቤቱን ፕሬዝዳንት የመምረጥ መብት አላቸው::[74]

አንድ ጉዳይ ወደዚህ ፍ/ቤት ሲመጣ ጉዳዩ የሚታየው እና ውሳኔ የሚሰጠው ፕሬዝደንቱና ቢያንስ ሁለት ዳኞች ባሉበት ይሆናል::[75] ሌላው ከዚህ ጋር ተያይዞ ሊታይ የሚገባው በፍ/ቤቱ የሚሰጡ ውሳኔዎች አፈጻጸም ጉዳይ ሲሆን፤ ውሳኔው ሊፈጸም የሚችለው በቤተክርስቲያኗ ጳጳስ ተቀባይነትን ካገኘ ነው:: በጳጳሱ ተቀባይነት ካላገኘ የፍ/ቤቱ ውሳኔ ያን ያክል ትርጉም ያለው አይሆንም፤ ተፈጻሚነትም አያገኝም:: ነገር ግን ጳጳሱ በራሳቸው የመሰላቸውን በመወሰን ለዚያ ጉዳይ ጊዜያዊ እልባት መስጠት ይችላሉ፤ ጉዳዩንም ለጠቅላይ ፍ/ቤት (General church court) ማቅረብ ይኖርባቸዋል::[76] ይህ ፍ/ቤት በጀቱን የሚያገኘው በአጥቢያው ካለችው ቤተክርስቲያን ነው::[77]

**ለ/ ጠቅላይ ፍ/ቤት (General Church Court) -** ይህ ፍ/ቤት በእርከን ደረጃ ከታች ወደ ላይ ሁለተኛው ደረጃ ፍ/ቤት ነው:: የዚህ ፍ/ቤት ዳኞች እንደ መጀመሪያ ደረጃው ፍ/ቤት ሁሉ ሊያሟላቸው የሚገቡ የቅጥር መመዘኛዎች አሉ::

---

[70] *The Statute of the Russian Orthodox Church*, Department for External Church Relations of the Moscow Patriarchate http://orthodoxeurope.org/page/3/15.aspx/ **አንቀጽ-1፤** የሩሲያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን የራሷ ሕግ አውጪ፣ ሕግ አስፈጻሚና ሕግ ተርጓሚ አካላት አሏት:: ሕግ የመተርጐምን ሥልጣን በቤተክርስቲያኗ ለተቋቋመው ሃይማኖታዊ ፍ/ቤት ሰጥታለች:: ሌሎች የቤተክርስቲያኗ ተቋሞችና ሰዎች ምንም ዓይነት ሕግ የመተርጎም ሥልጣን የላቸውም:: የሩሲያ ሕገ መንግሥትም ሆነ የሃይማኖት ሕግ መንግሥታዊ ሃይማኖት እንደሌለ እና የሃይማኖት ነጻነትና እኩልነትም የተጠበቀ መሆኑን ይደነግጋሉ፡፡ *የሩሲያ ፌደሬሽን ሕገ መንግሥት፣ አንቀጽ ፲፫፣፲፬፣፲፱፣፳፰።*

[71] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ ፱. ይህም በተለይ በቤተክርስቲያን ሕግ በሚገዙ (Canonican govrernance)፣ በቤተክርስቲያን ትዕዛዝ (Church order)፣ በቤተክርስቲያን ሥርዐት (Liturgican) እና (Pastorcr actiritien) ላይ ነው፡፡

[72] ዝኒከማሁ፣ አንቀጽ-፪፡፡

[73] ዝኒከማሁ፣ አንቀጽ-፲፡፡

[74] ዝኒከማሁ፣ አንቀጽ-፲፩-፲፪፡፡

[75] ዝኒከማሁ፣ አንቀጽ-፲፬፡፡

[76] ዝኒከማሁ፣ አንቀጽ-፲፮፡፡

[77] ዝኒከማሁ፣ አንቀጽ-፲፯፡፡

በዋናነት በዚህ ፍ/ቤት ዳኛ ለመሆን ይህ ሰው ኤጲስ ቆጶስ ሊሆን ይገባል፤ የጳጳሳትን ም/ቤት ይሁንታንና ፈቃድም ማግኘት አለበት:: ይህ ፍ/ቤት ፬ ዓመት የሥራ ዘመን ያላቸው አንድ ፕሬዝዳንትና ቢያንስ ፬ ዳኞች ይኖረዋል:: ሌላው ደግሞ ምንም እንኳን የጳጳሳትን ም/ቤት ዳኞችን ፕሬዝዳንቱ የመሾም ሥልጣን ቢኖረውም ዳኞች በዚህ የሥልጣን ዘመናቸው በተለያዩ ምክንያቶች ሥራቸውን ከለቀቁ የሞስኮ ፓትርያርክ ቅዱስ ሲኖዶስ እና የሁሉም ሩሲያዊ ምእመናን ጉባኤ በጋራ ተጠባባቂ ፕሬዝዳንት ወይም ሌላ ዳኛ በመቅጠር እና ክፍተቱን የመሙላት መብት አላቸው::[78]

የዚህ ፍ/ቤት ውሳኔዎች ተፈጻሚነት የሚያገኙት በሞስኮው ፓትርያርክ በሁሉም ሩሲያዊ ምእመናን እና በቅዱስ ሲኖዶስ በጋራ ሲጸድቁ ብቻ ነው:: በውሳኔው ላይ ቅሬታ ካላቸው የፍ/ቤቱን ውሳኔ ወደ ጐን በመተው የራሳቸውን ውሳኔ እንዲፈጸም ያደርጋሉ:: ነገር ግን ቅሬታ ወይም ውዝግብ ያስነሳው ጉዳይ ወደ ይግባኝ ሰሚው ጳጳሳት ም/ቤት ፍ/ቤት እንዲቀርብ ይደረጋል::[79]

ይህ ፍ/ቤት በእርከን ደረጃ ከታች ወደ ላይ ሁለተኛ ስለሆነ፤ በመጀመሪያ ደረጃው ሃይማኖታዊ ፍ/ቤት የሚሠሩ ሥራዎችን የመከታተል ሥልጣን አለው:: ሥራውን ለመሥራት የሚያገለግለውን በጀት ደግሞ ከሀገሪቱ አጠቃላይ የቤተክርስቲያን በጀት ያገኛል::[80]

**ሐ/ የጳጳሳት ም/ቤት ፍ/ቤት** **/Court of Bishops Council/** ይህ ፍ/ቤት በሩሲያ ኦርቶዶክስ ሃይማኖታዊ ፍ/ቤት አወቃቀር መሠረት የመጨረሻውና ይግባኝ ሰሚ ሃይማኖታዊ ፍ/ቤት ነው::[81] ሥራዎቹም የሚከናወኑት በጳጳሳቱ ም/ቤት ነው፡፡ ይህ ፍ/ቤት እንደ ሌሎቹ ሃይማኖታዊ ፍ/ቤቶች ፕሬዝዳንትና ሌሎች አባላት አሉት:: ለሌሎች ሃይማኖታዊ ፍ/ቤቶች ሥራዎች የሚከፋፈሉት በዚህ ፍ/ቤት አባላት ነው::[82]

በአጠቃላይ የሩሲያ ሃይማኖታዊ ፍ/ቤቶች ምንም እንኳን እንደ አወቃቀራቸው ልዩነት ቢኖራቸውም የጋራ ባሕርያትም አላቸው:: ለምሳሌም የዳኝነት ክፍያ ክርክርን በዝግ ችሎት ማካሔድ ውሳኔዎች በጳጳሱ ወይም በጳጳሳቱ ም/ቤት ተቀባይነትን ያገኙ ትእዛዞች፣ ጥያቄዎች፣ መጥሪያዎችና ሌሎች የፍ/ቤት ደብዳቤዎች በሁሉም ካህንና ምእመን ላይ አስገዳጅ መሆናቸው መጥቀስ ይቻላል:: ሌላው አንድ የሚያደርጋቸው ደግሞ በሃይማኖታዊ ቅጣት ዙሪያ ነው:: ይህም እነዚህ ሃይማኖታዊ ፍ/ቤቶች አንድን አገልጋይ ለዕድሜ ልክ ማገድና ማውገዝ የመሳሰሉ ቅጣቶችን መጣል አይችሉም:: እነዚህ ቅጣቶች ሊጣሉ የሚችሉት በእነዚህ ሃይማኖታዊ ፍ/ቤቶች አቅራቢነት ፍ/ቤቱ ባለበት ያሉት የቤተክርስቲያኗ ጳጳስ ወይም በሞስኮው ፓትርያርክ እና በቅዱስ ሲኖዶስ ነው::[83]

---

78 ዝኒከማሁ፣ አንቀጽ-፲፰,፲፱,፳፩፡፡

79 ዝኒከማሁ፣ አንቀጽ-፳፫፡፡

80 ዝኒከማሁ፣ አንቀጽ-፳፬፡፳፭፡፡

81 ዝኒከማሁ፣ አንቀጽ-፳፮፡፡

82 ዝኒከማሁ፣ አንቀጽ-፳፰፡፡

83 ዝኒከማሁ፣ አንቀጽ-፯፡፭፡፱፡፰፡፡

**፬.፪. የእስራኤል ልምድ፣** በእስራኤል የሚገኙ ፍ/ቤቶች የተለያየ ዓይነት አወቃቀር ይከተላሉ፡፡[84] እነዚህ የተለያዩ ፍ/ቤቶች እንደ አወቃቀራቸው በአስተዳደር በኩልም ተ ጠሪነታቸው ለተለያዩ አካላት ነው::[85] በመሆኑም በፍትሕ ማስፈን እንቅስቃሴው ውስጥ ፍ/ቤቶች ከሌሎች አካላት  እንዲሁም ባለሥልጣናት ጣልቃገብነት እና ተጽእኖ ነጻ ናቸው:: እነዚህ ፍ/ቤቶች የራሳቸው የሆነ መለያ ባሕርይና ሥልጣን አላቸው::[86] እስራኤል ውስጥ  የአይሁዳውያን፣ የራብኒካል፣ የክርስቲያኖች የሙስሊሞች ሃይማኖታዊ ሕጎችና ፍ/ቤቶች ሲኖሩ፤ ለዚህ ጽሑፍ ዓላማ ግን የራብኒካል ፍርድ ቤቶችን ልምድ ብቻ እናያለን::[87]

***ሀ/ የራብኒካል ፍ/ቤት ዳኞች አቀጣጠርና የሥራ ዘመን*** *በእስራኤል የሃይማኖታዊ ፍ/ቤቶች እያንዳንዱ የራብነኪኒካል ፍ/ቤት ዳኞች የሚሾመው በእያንዳንዱ በአይሁድ እምነት ተከታይ ማኅበረሰብ ነው::[88] አንድ በሃይማኖት ፍ/ቤት የሚሠራ ዳኛ ከተቀጠረ በኋላ በምንም ዓይነት ሁኔታ የሕግ አውጪውም ሆነ የሕግ አስፈጻሚው አካል ያንን ዳኛ ሊያነሣ መብት የለውም:: ነገር ግን አንድ ዳኛ በሞት፣ በራስ ፍላጎት፣ በጡረታ /70 ዓመት/ እና በዲሲፕሊን ብቻ ከሥራው ሊሰናበት እንደሚችል በግልጽ ተቀምጧል፡፡*[89]

*ከዚህ በተጨማሪ የራብኒካል ፍ/ቤት ዳኞች ደመወዛቸውን  ከእስራኤል መንግሥት ያገኛሉ፤ ፍ/ቤቱም አገልግሎት የሚሰጡት  በመንግሥት ሕንፃዎች ውስጥ ነው፡፡ ብዙ ጊዜ ዳኞቹ በጸታ ወንዶችና የአይሁድ መምህራን ናቸው::*[90]

**ለ/ በራብኒካል ፍ/ቤት የሚታዩ ጉዳዮች** በአሁኑ ሰዓት በእስራኤል ራብኒካል ፍ/ቤቶች በጋብቻና በፍቺ ጉዳዮች ላይ ብቻ የመዳኘት ሥልጣን አላቸው ለማለት ቢያስደፍርም ከፍቺ ጋር ተያይዘው ለሚነሡ የሕፃናት አያያዝ እና በንብረት ክፍፍል ዙሪያ የመደበኛ ፍ/ቤቶች ከራብኒካል ፍ/ቤቶች ጋር የጐንዮሽ ሥልጣን አላቸው::[91] ሁለቱም ፍ/ቤቶች በፍቺ ዙሪያ በፍትሐ ብሔር ሕጉ ውስጥ የበለጠ ክብደት ወይም ዕውቅና የተ ሰጠው ልማድ ከሌለ በቀር የአይሁድ ሃይማኖታዊ ሕጐችን እንዲከተሉ ታዝዘዋል፡፡

---

[84] እ.ኤ.አ በ፲፱፻፺፪ በእስራኤል የወጣው የፍ/ቤቶች ሕግ በእስራኤል የሚገኙ ፍ/ቤቶችን በ፫ መንገድ አዋቅሮአቸዋል:: እነርሱም የመደበኛ ፍ/ቤቶች፣ የሃይማኖት ፍ/ቤቶችና ወታደራዊ ፍ/ቤቶች ናቸው:: በርግጥ ከእነዚህ ፍ/ቤቶች በተጨማሪ የ፲፱፻፺፪ቱ ሕግ ሌሎች ልዩ ፍ/ቤቶችንም አቋቁሟል:: ለምሳሌ የሠራተኛ፣ የኢንሹራንስ፣ የትራፊክና፣ የወጣቶች ልዩ ፍ/ቤቶችን መጥቀስ ይቻላል:: ምንም እንኳን ግልጽ የሆነ ሕገ መንግሥት ባይኖራትም መሠረታዊው የእስራኤል ሕግ ሀገሪቷን አይሁዳዊት ዲሞክራት ሀገር ስለሚላት የአይሁድ እምነት ብሔራዊ ሃይማኖት ነው፡፡ ነገር ግን ሀገሪቷ በግልጽ ለሌሎች ሃይማኖቶች እውቅና ሰጥታ፤ የሃይማኖት ነጻነትም የሚከበርባት ሀገር ናት፡፡ Daphne Barak-Erez, Religion and The Secular State – An Israeli Case Study, prepared for the “Religion and the Secular State: panel at the conference of the International Academy of Comparative Law, Washington DC, 2010.

[85] Http//countrystudies.us/israel/84.htm/ *የመደበኛ ፍ/ቤቶች ተጠሪነታቸው ለፍትሕ ሚኒስቴር፣ ሃይማኖታዊ ፍ/ቤቶች ለሃይማኖታዊ ጉዳዮች ሚኒስቴር እና ወታደራዊ ፍ/ቤቶች ደግሞ ተጠሪነታቸው ለሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ነው::*

[86] ዝኒ ከማሁ፡፡ በተለይ የ፲፱፻፶፫ቱ እ.ኤ.አ ዳኞች ሕግ፣ የ፲፱፻፶፯ቱ እ.ኤ.አ የፍ/ቤቶች ሕግ፣ የ፲፱፻፶፫ቱ እ.ኤ.አ የራብኒካል ፍ/ቤቶች ሥልጣን ሕግ፣ የ፲፱፻፶፭ቱ እ.ኤ.አ የዳዩኒም ሕግ፣ የ፲፱፻፷፩ዱ እ.ኤ.አ ቃዲስ ሕግ፣ የ፲፱፻፷፱ቱ እ.ኤ.አ በጋብቻ ጉዳዮች ላይ የሚያጠናውን ሕግ እና የ፲፱፻፸፱ የፍ/ቤቶች ሕግ የእነዚህ ፍ/ቤቶች ልዩ ባሕሪ እና ሥልጣን መነሻዎች እንደሆኑ ይቀመጣል::

[87] Aharon Barak, *Some Reflections on the Israeli Legal System and its Judiciary*, President of the Supreme Court of Israel delivering lecture at the Fifth Conference of the Ius Commune Research School, (Leuven, 23 November 2000); at 2 http://www.ejcl.org/61/art61-1.pdf

[88] ዝኒ ከማሁ፡፡

[89] Rochelle Furstenber, *The Flourishing of Higher Jewish Learning for Women*, (No. 429  26 Nisan 5760 /1 May 2000); www.jcpa.org

[90] Daphna Hacker, *supra note* 62, p.6.

[91] Frances Rada, *Secular Constitutionalism Vindicate*, Cardozo Law Review, (Vol. 30, 2009); p. 2782.

ወደ ሥነ ሥርዐትና ማስረጃ ሕግ ስንመጣ ግን ሁለቱም ፍ/ቤቶች የተለያየ ሥርዐትን ይከተላሉ:: ለምሳሌ ራብኒካል ፍ/ቤቶች በሃይማኖታዊ ሕጋቸው የተቀመጡትንና እውቅና የተሰጣቸውን የሥነ ሥርዐትና ማስረጃ ሕግጋት ሲከተሉ መደበኛ ፍ/ቤቶች ግን በፍትሐ ብሔር ሕጋቸው የተቀመጠውን ይከተላሉ:: ነገር ግን የእስራኤል ጠቅላይ ፍ/ቤት ራብኒካል ፍ/ቤቶችን የፍትሐ ብሔር ሕጎችን (በተለይም የሴቶችን እኩልነትን እንዲከበሩ ለማስቻል) እንዲያከብሩ በተደጋጋሚ እያሳሰበ ይገኛል::[92]

**፬.፫. በአሜሪካ የኢፒስኮፓል ቤተክርስቲያን** **(Episcopal Church)**፣ በአሜሪካ የሕግ ሥርዐት ሃይማኖታዊ ፍርድ ቤቶች እውቅና ተሰጥቷቸው ጉዳዮችን የሚያዩ ሲሆን መደበኛ ፍ/ቤቶች ሥልጣን በሌላቸው መንፈሳዊ ጉዳዮች ላይ ይዳኛሉ:: በጥቂቱም ከሌሎች ሀገሮች ለየት ያለውንና ለእኛ ሀገር ጠቃሚ የሆነውን የኢፒስኮፓል ሃይማኖታዊ ፍ/ቤት አሠራር ማየት መርጠናል:: ይህ ፍርድ ቤት ማናቸውንም ካህናትን የሚመለከት የዲሲፕሊን ጉዳይ የማየት ሥልጣን ሲኖረው ሁለት ዓይነት ስልት ይከተላል:: የመጀመሪያው አካል ጳጳሳትን የሚመለከት ክስ ሲሆን ጳጳሳትን ብቻ በአባልትነት በያዘ ፍ/ቤት ይታያል:: በዚህ ፍ/ቤት ውሳኔ ቅር የተሰኘ ይግባኙን ለይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት (Court of Review) ማቅረብ ይቻላል::

ሁለተኛው አካል ደግሞ የቀሳውስትንና የዲያቆናትን ጉዳይ የሚመለከት ነው:: ክሱ መጀመሪያ መቅረብ ያለበት በእያንዳንዱ አጥቢያ ቤተክርስቲያን ለተቋቋመው መንፈሳዊ ፍ/ቤት ነው:: በዚህ ፍ/ቤት ውሳኔ ቅር የተሰኘ በክፍለ ሀገር ደረጃ ለተቋቋመው ይግባኝ ሰሚ መንፈሳዊ ፍ/ቤት ጉዳዩን ማቅረብ ይቻላል:: የአጥቢያ መንፈሳዊ ፍ/ቤት ክህነት የሌላቸውን ሰዎች፣ ቀሳውስትን ወይም ዲያቆናትን እና በአብላጫ ድምፅ ያሸነፈን ካህን በአባልትነት የያዘ ነው:: ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ደግሞ አንድ ጳጳስ ፣ሦስት ቀሳውስት ወይም ዲያቆናት እና ክህነት የሌላቸውን ሰዎች ሦስት በአባልትነት የያዘ ነው::[93] በሁለቱም ስልቶች ክስ መጀመሪያ የሚቀርበው ለመጀመሪያ መርማሪ ኮሚቴ (Initial Review Committee) ነው:: የዚህ ኮሚቴ ዋነኛ ሥራ በወንጀል ክስ ላይ እንዳሉት ጁሪዎች (Jury) ነው::[94]

---

[92] Daphna Hacker, *supra note* 90, ገጽ.7፤ ዝኒ ከማሁ እስራኤል ከ፲፮ኛው መ/ክ/ዘ ጀምሮ ለ፬፻ ዓመታት ያክል በኦቶማን ቱርክ ግዛት ውስጥ ነበረች:: ከዚያም በኋላ ከ፲፱፻፲፰- ፲፱፻፵፰እ.ኤ.አ በእንግሊዝ ሞግዚትነት ስትተዳደር ነበር:: በእነዚህ ጊዜያቶች የይሁዳ ክርስቲያኖች በግል ጉዳዮች ላይ የራሳቸውን ሃይማኖታዊ ፍ/ቤት እንዲያቋቁሙ ተፈቅዶላቸው በራሳቸው ሃይማኖታዊ ፍ/ቤቶች ሲገለገሉ ቆይተዋል:: ይህ የአሠራር ሥርዐትም ሚሌት ይባላል:: ይህ ሥርዐት በእንግሊዝ የሞግዚት አስተዳደር ወቅትም ቀጥሎ ነበር:: ታዲያ እነዚህ የአይሁድ ሃይማኖታዊ /ራብኒካል/ ፍ/ቤቶች እስከዚህ ወቅት ድረስ በጋብቻ ወይም በፍቺ ጉዳይ ባል ሚስቱን ሲፈታ ሊሰጠው ስለሚገባ አበል፣ የቀለብ አሰፋፈር፣ ለሕፃን ልጅ ሞግዚት በተመለከተ፣ጉዲፈቻ፣ በሕግ ችሎታ በሌለው ሰው ንብረቶች ዙሪያ፣ በውርስ፣ ኑዛዜ እና በጠፋ ሰው ንብረቶች አስተዳደር ዙሪያ የመዳኘት ሥልጣን አላቸው::

ነገር ግን እስራኤል እንደ ሀገር መቋቋም ከጀመረችበት ጊዜ ጀምሮ የራብኒካል /ሃይማኖታዊ/ ፍ/ቤቶች ሥልጣን በእስራኤል ሕግ አውጪ አካል እና ጠቅላይ ፍ/ቤት እየተቀነሰ ለሌላ ተሰጥቶባቸዋል:: ለምሳሌ በአሁኑ ወቅት በሕግ ችሎታ የሌለው እና የጠፋ ሰውን ንብረቶች በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ የራብኒካል ፍ/ቤቶች እንደ ከዚህ ቀደሙ ሥልጣን የላቸውም:: በሕግ ለሌላ ፍ/ቤት ተሰጥተዋል:: በጉዲፈቻ እና በውርስ ጉዳዮች ዙሪያ ራብኒካል ፍ/ቤቶችም ሆነ መደበኛ ፍ/ቤቶች ሥልጣን አላቸው፤ ሆኖም በተከራካሪዎቹ ፈቃድ ላይ የተመሠረተ ነው:: ነገር ግን በእነዚህ ጉዳዮች ዙሪያ በሁለቱ ፍ/ቤቶች ግጭት ከተነሣ መደበኛ ፍ/ቤቶች ቅድሚያ እንደሚሰጣቸው ሕጉ በግልጽ አስቀምጧል::

[93] ዝኒ ከማሁ::

[94] ዝኒ ከማሁ::

**፬.፬ የእንግሊዝ አንግሊካል ቤተክርስቲያን፣**የእንግሊዝን ልምድ በምናይበት ወቅት ደጋሞ በሕግ እውቅና ተሰጥቷቸው እየሠሩ የሚገኙት የክርስቲያን ሃይማኖታዊ ፍ/ቤቶች (Anglical Courts) ብቻ ናቸው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የራብኒካል እና ሸሪአ ሃይማኖታዊ ፍ/ቤቶች (ምንም እንኳን ውዝግብ ያስነሣ ጉዳይ ቢሆንም) በመንግሥት ውሳኔ መሠረት ግላዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ብቻ ሥልጣን ተሰጥቷቸዋል፡፡ በእንግሊዝ የሽምግልና ሕግ መሠረት ሥራቸውን እያከናወኑ ነው፡፡ በዚህም የሕግ ማዕቀፍ ጉዳዩን ማየት ያለባቸው በሁሉም ተከራካሪ ወገኖች ፈቃድ ብቻ መሆን እንዳለበት ተቀምጧል፡፡ ስለሆነም በእንግሊዝ የሚገኙ ሃይማኖታዊ ፍ/ቤቶች (የክርስቲያን ሃይማኖታዊ ፍ/ቤቶች - Anglical Courts በስተቀር) የሚሰጧቸው ውሳኔዎች ፍትሐ ብሔራዊ ሽምግልና ይዘት አላቸው፡፡[95]

**፬.፭. የሸሪአ ፍ/ቤቶች በኢትዮጵያ፣**የሸሪአ ፍ/ቤቶች በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ በሕግ እውቅና አግኝተው የተቋቋሙት በዐፄ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥት በ፲፱፻፵፬ዓ.ም በዐዋጅ ቁጥር ፲፪ ነው፡፡[96] ከሁለት ዓመት በኋላ በ፲፱፻፵፮ የቃዲስ ፍ/ቤቶች ማቋቋሚያ ዐዋጅ ቁጥር ፲፪ በቃዲስ እና ናኢባ ም/ቤቶች ማቋቋሚያ ዐዋጅ ቁጥር ፷፪ ተሻረ፡፡ ይህ ዐዋጅ ከ፲፱፻፵፬ቱ ዐዋጅ በተለየ ሦስት ፍ/ቤቶችን አቋቁሟል፡፡[97] ነገር ግን በ፲፱፻፺፪ የወጣውን የፌደራል ሸሪአ ፍርድ ቤቶችን አቋም ለማጠናከር የወጣውን ዐዋጅ ቁጥር ፩፻፹፷/፲፱፻፺፪ በምንመለከትበት ወቅት የሸሪአ ፍርድ ቤቶች አወቃቀር የተለየ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ በዚህ ዐዋጅ መሠረት የፌደራል ሸሪአ ፍርድ ቤቶች ተጠሪነታቸው ለፌደራል ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ሆኖ የመደበኛ ፍርድ ቤቶችን አወቃቀር በመከተል የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ የሸሪአ ፍርድ ቤት፣ የፌደራል ከፍተኛ ሸሪአ ፍርድ ቤት እና የፌደራል ጠቅላይ ሸሪአ ፍርድ ቤት አቋቁሟል፡፡[98]

### ሀ/ የፍ/ቤቶቹ አወቃቀርና የዳኝነት ሥልጣን

**የፌደራል ጠቅላይ ሸሪአ ፍርድ ቤት:** የፌደራል ከፍተኛ ሸሪአ ፍርድ ቤት በይግባኝ ሰሚ ወይም በመጀመሪያ ደረጃ የመዳኘት ሥልጣኑ በሰጣቸው ውሳኔዎች ወይም ጉዳዮች ላይ በይግባኝ ውሳኔ የመስጠት ሥልጣን አለው፡፡ ይህ ፍ/ቤት ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ አንድ ዋና እና ምክትል ዋና ቃዲ እንዲሁም ሌሎች ቃዲዎችና ሬጅስትራሮች ሲኖሩት፤ ጉዳዮችን በአንድ ሰብሳቢና በሁለት ቃዲዎች ያያሉ፡፡[99]

**የፌደራል ከፍተኛ ሸሪአ ፍርድ ቤት፡** ግምታቸው ከ200000 ብር በላይ በሆኑ ጉዳዮች፣ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪአ ፍርድ ቤት በመጀመሪያ ደረጃ የመዳኘት ሥልጣኑ በሰጣቸው ውሳኔዎች ላይ በይግባኝ ውሳኔ የመስጠት እና አንድን ጉዳይ ከአንድ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪአ ፍርድ ቤት ወደ ሌላ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪአ ፍርድ ቤት የመቀየር ሥልጣን አለው፡፡ ይህ ፍ/ቤት ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ አንድ ተጠሪ እንዲሁም ሌሎች ቃዲዎችና ሬጅስትራሮች ሲኖሩት ጉዳዮችን በአንድ ሰብሳቢና በሁለት ቃዲዎች ያያል፡፡[100]

---

[95] Nick Tarry, *Religious Courts Already In Use,* (*BBC News,* February 12, 2008); http://news.bbc.co.uk/2/hi/uk_news/7233040.stm

[96] Abdul Wasie, *Sharia courts in Ethiopia: Their Status, Organization And Functions* (Addis Ababa, Haile Sellassie I University Press,1971); pp.15. ይህ ዐዋጅ ሁለት ዓይነት ፍ/ቤቶችን አቋቁሟል፡፡ እነርሱም የቃዲስ ፍ/ቤት እና ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት (የሸሪያት ፍ/ቤት) ናቸው፡፡

[97] ዝኒ ከማሁ፣ ከገጽ 24-28፡፡ ይህ ዐዋጅ ሦስት አይነት ፍ/ቤቶችን አቋቁሟል፡፡ እነርሱም የናኢባ ም/ቤት፣ የቃዲስ ም/ቤት እና የሸሪአ ፍ/ቤት ናቸው፡፡

[98] የፌደራል ሸሪአ ፍ/ቤቶችን አቋም ለማጠናከር የወጣ ዐዋጅ ቁጥር ፩፻፹፰/፲፱፻፺፪፣ አንቀጽ ፫፡፡

[99] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ ፰፣፲፩፡፡

[100] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ ፱፣፲፪፡፡

***የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪአ ፍርድ ቤት፡*** *ግምታቸው ከ200000 ብር በታች በሆኑ እና በገንዘብ ሊተመኑ በማይችሉ ጉዳዮች ላይ የመዳኘት ሥልጣን አለው፡፡ እንደ ፌደራሉ ከፍተኛ ሸሪአ ፍርድ ቤት ይህ ፍ/ቤት ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ አንድ ተጠሪ እንዲሁም ሌሎች ቃዲዎችና ሬጅስትራሮች ሲኖሩት ጉዳዮችን በአንድ ቃዲዎች ያያል፡፡*[101]

## ለ/ የፌደራል ሸሪአ ፍርድ ቤቶች አሠራር

*አሁን በሥራ ላይ ባለው ዐዋጅ ቁጥር ፩፻፹፰ አንቀጽ ፩ እና በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፸፰(፭) መሠረት የፌደራል ሸሪአ ፍርድ ቤቶች የመዳኘት ሥልጣን የሚኖራቸው በተከራካሪዎቹ ሙሉ ፈቃድ ብቻ ነው፡፡ የበፊቶቹ ዐዋጆች ማለትም የ፲፱፻፹፰ቱ እና የ፲፱፻፹፯ቱ ግን ይህን ጉዳይ በግልጽ ስላላስቀመጡት በአሠራር ላይ ትልቅ ችግር ፈጥሮ ነበር፡፡*

*የፌደራል ሸሪአ ፍርድ ቤቶች ሥራቸውን የሚያከናውኑትና ጉዳዮችንም የሚመረምሩት የሸሪአን ሕግ በመከተል ሲሆን ሥነ ሥርዐትን በተመለከተ ግን የፍትሐ ብሔር ሥነሥርዐት ሕግን ይከተላሉ፡፡ ሥራቸውን በግልጽ ችሎትና በአማርኛ ቋንቋ የሚያከናውኑ ሲሆን በጀታቸውን የሚያገኙት ከፌደራል መንግሥት ከሚገኝ ድጎማ እና ከሌሎች ድጋፍ ሰጭ ምንጮች ነው፡፡*[102]

*የሁሉም የፌደራል ሸሪአ ፍርድ ቤት ዳኞች /ቃዲዎች/ አሿሿም ተመሳሳይ ነው፡፡ ይኸውም በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት አቅራቢነት በዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ነው፡፡ የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ጥያቄውን ለእስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ጉባኤ ያቀርባል፡፡ የእስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ጉባኤ ሰብሳቢ በጉባኤው ተጠቁመው አብላጫ ድምፅ ያገኙትን እጩዎች ከአጭር የሕይወት ታሪካቸው ጋር ለዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ያቀርባል፡፡ የቃዲዎች የዲሲፕሊን ግድፈቶች የሚታረሙትና የሚወስኑት በፌደራል ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ዐዋጅ እና በፌደራል ዳኞች መተዳደሪያ ደንብ መሠረት ነው፡፡*[103] *ምንም እንኳን በዚህ ሥር የታዩት የፌደራል ሸሪአ ፍ/ቤቶች ቢሆኑም በየክልሎቹም ተመሳሳይ አወቃቀር ይዘው የተቋቋሙ የሸሪአ ፍ/ቤቶች ይገኛሉ፡፡*

*በአጠቃላይ ከዚህ በላይ ያየናቸው ሀገሮች ልምድ የሚያሳየው  ከመደበኛ ፍ/ቤቶች በተ ጨማሪ ሌሎች ልዩ ሃይማኖታዊ ፍ/ቤቶች በሕግ እውቅና አግኝተው እየሠሩ መሆናቸውን ነው። እነዚህ ሃይማኖታዊ ፍ/ቤቶች ከመደበኛ ፍ/ቤቶች በተለይ የራሳቸው የሆነ የዳኝነት ሥልጣን አወቃቀር ፣አሠራርና የዳኞች አሿሿም ሥርዐት አሏቸው። በተለይም በአብዛኞቹ ሀገሮች ሃይማኖታዊ ፍ/ቤቶች በጋብቻና ፍቺ እንዲሁም መደበኛ ፍ/ቤት ሊታዩ በማይችሉ ሌሎች ሃይማኖታዊ መሠረት ባላቸው ጉዳዮች ላይ ሥልጣን አላቸው።*

*ስለዚህ ከነዚህ ሀገሮች ልምድ በመነሳት ኢትዮጵያም ከመደበኛ ፍ/ቤቶች በተጨማሪ የራሳቸው የሆነ አወቃቀር አሠራር፤ የዳኝነት ሥልጣንና የዳኞች አሿሿም ሥርዐት የሚከተሉ የኦርቶዶክስ ሃይማኖታዊ ፍ/ቤቶችን ማቋቋም ትችላለች።*

[101] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ ፲፡፲፪፡፡
[102] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ ፯፡፲፱፡፡
[103] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ ፲፯፡፲፰፡፡

 © ጥናትና ምርምር ማእከል፣ ማኅበረ ቅዱሳን

## ፭. ማጠቃለያና የመፍትሔ ሐሳቦች

በቀደመው የኢትዮጵያ ታሪክ፤ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን መንፈሳዊ ፍ/ቤቶች እንደ ዘመናዊ ፍ/ቤት ተዋቅረው ባይሠሩም እንኳ፤ በብዙ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ ሲሰጡ የነበሩ ተቋማት ናቸው:: ለመጀመሪያ ጊዜም በመደበኛ ሕግ ውስጥ እንዲደራጁ የሕግ እውቅና የተሰጣቸው በ፲፱፻፴፭ ዓ.ም. በወጣው ደንብ ነበር:: ነገር ግን በዘመኑ ተጠናክረው የቀጠሉበትና በዘመናዊ የፍትሕ ሥርዐት ውስጥ አገልግሎት የሰጡበት ጊዜ የለም:: በተለይም በ፲፱፻፶፪ ዓ.ም የወጣው የፍትሐ ብሔር ሕግ የመንፈሳዊ ፍ/ቤቶችን ህልውና አደጋ ላይ ጥሎታል:: ይሁን እንጂ ምንም እንኳ የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ በመደበኛ ሕግ የተቋቋመ መንፈሳዊ ፍ/ቤት ባይኖራትም በቤተክርስቲያኗ ውስጥ የሚነሡ ጉዳዮችን አይቶ ውሳኔ የሚሰጥ አካል በ፲፱፻፺፩ ዓ.ም ለሦስተኛ ጊዜ ተሻሽሎ በወጣው ሕገ ቤተክርስቲያን (ቃለ ዓዋዲ) አቋቁማ ራሷን ስታስተዳድር ኖራለች:: በዚህ ቃለ ዓዋዲ የተቋቋመው አካል ግን በአወቃቀርም ሆነ በአሠራር ክፍተት ያለበት ነው:: በመጨረሻም በ፲፱፻፹፯ቱ ሕገ መንግሥት ሃይማኖታዊ ፍ/ቤቶች ሊሠራባቸው እንደሚችል በሕግ ሊቋቋሙ እንደሚችሉ፤ ተከራካሪ ወገኖችም በሃይማኖታዊ ፍ/ቤቶች ቤተሰባዊና ግላዊ ጉዳያቸውን የመዳኘት መብት እንዳላቸው ተደንግጓል::

ምንም እንኳን ሕገ መንግሥቱ በግልጽ ሃይማኖታዊ ፍ/ቤቶች እንደሚቋቋሙ ቢደነግግም፤ እስከ አሁን ድረስ የኢትዮጵያ ኦ/ተ/ቤ/ክ መንፈሳዊ ፍ/ቤት ባለመቋቋሟ በሕግ ሥርዐቱም ሆነ በፍትሕ አስተዳደሩ ውስጥ ችግር ማስከተሉ አልቀረም:: ይህም በመደበኛ ሕጉ ላይ ክፍተትን፣ በፍ/ቤቶችም ጫናን፣ ያለ ዕውቀት ውሳኔ መስጠትን፣ በቤተክርስቲያኗ ላይ ደግሞ የውስጥ ጉዳይን የመወሰን ነጻነት ማጣትንና የሌላ ወገን ጣልቃ ገብነትን ስታስተናግድ፤ በአገልጋዮቿ ላይ ደግሞ ግራ መጋባትንና ፍትሕ የሚያገኙበትን ትክክለኛ ፍ/ቤት ማጣትን አስከትሏል::

በአንጻሩም ደግሞ የቤተክርስቲያኗ መንፈሳዊ ፍ/ቤት መቋቋም ሕገ መንግሥቱ ያለመውን ግብ ሊያሳካ የሚችልና ከሕገ መንግሥቱ ጋር የማይቃረን፣ ከላይ የዘረዘርናቸውን (ማለትም በሕጉ፣ በመደበኛ ፍ/ቤቶች፣ በቤተክርስቲያኗ እንዲሁም በአገልጋዮች) ለሚፈጠሩት ችግሮች ዋነኛና አግባባዊ መፍትሔ ነው:: ይህ የመንፈሳዊ ፍ/ቤት መቋቋም በኢትዮጵያ የተጀመረ ሳይሆን በሥልጣኔ ገፍተዋል በሚባሉት እንደ አሜሪካ፣ እንግሊዝ ፣ ሩሲያ፣ ጣሊያን ወዘተ ተቀባይነት ኖሮት የሚሰራበት ነው:: ስለሆነም ከላይ የተጠቀሱትን ችግሮች ለማስወገድ፣ የታሰበውን ውጤት ለማግኘትና ሕገ-መንግሥቱም እውቅና የሰጠውንና ሊጠብቀው ያሰበውን ግብ ለማሳካት እነዚህ መንፈሳዊ ፍ/ቤቶች በቶሎ ሊቋቋሙ ይገባል::

### የመፍትሔ ሐሳቦች

#### ሀ/ መንግሥት

1. የመንፈሳዊ ፍ/ቤቶችን አስፈላጊነት፣ ለሕግ ሥርዐቱ ማደግም ሆነ ለፍትሕ መስፈን ከፍተኛ አስተዋጽኦ ስላላቸው ፍ/ቤቶች በቶሎ ቢያቋቁም፤
2. መደበኛ ፍ/ቤቶች የቤተክርስቲያንን ውስጣዊ አሠራር ሥርዐትና ቀኖና የሚመለከቱ ጉዳዮችን ከማየት/ከመዳኘት ቢቆጠቡ ፤

#### ለ/ ቤተክርስቲያን

1. ውስጣዊ አሠራሯን፣ ሥርዐቷን፣ ዶግማዋን የሚመለከቱ ጉዳዮችን ወደ መደበኛ ፍርድ ቤት እንዳይሔዱ ማድረግ ይልቁንም አማራጭ የክርክር መፍቻ መንገዶችን ብትጠቀም፤

2. እነዚህ መንፈሳዊ ፍ/ቤቶች በሕግ እውቅና ተሰጥቷቸው እስኪቋቋሙ ድረስ ያሏትን አደረጃጀት ማጠናከርና የሥነ ምግባር ክፍሎችን አጠናክራ ብትቀጥል፤
3. ቤተክርስቲያኗ ያሏትን መሠረታዊና የሥነ ሥርዐት ሕግጋት እስከ አሁን ይሠራባቸው ከነበረው በተሻለና በተጠናከረ ሁኔታ ተግባራዊ ብታደርግ፤
4. መንፈሳዊ ፍ/ቤቶች እንዲቋቋሙ ያላሰለሰ ግፊት ብታደርግ፤ ሊቃውንትን፣ ምእመናንን ስለመንፈሳዊ ፍ/ቤት ምንነትና አስፈላጊነት እንዲረዱ ብታደርግ

## ሐ/ የቤተክርስቲያን ሊቃውንትና ምእመናን

1.የቤተክርስቲያኗ የውስጥ ጉዳይ የሆኑትን ክርክሮች እያወቁ ወደ መደበኛ ፍ/ቤት ከመውሰድ ይልቅ የቤተክርስቲያኗ ባዘጋጀችው ክፍል ውስጥ ጉዳያቸው እንዲታይላቸው ቢጠይቁ፤
2. በተለይ የቤተክርስቲያኗ መሠረታውያንና ሥነ ሥርዐት ሕጎችን በማብራራትና፣ በመተርጎም ለምእመናንም እንዲያውቁት ብታስተምር እና በሕግጋቱ ውስጥ ስላሉት ሕጎች ማብራሪያ ቢጽፉ፤
3. መንፈሳዊ ፍ/ቤቱ ሊቋቋም የሚችልበትን አማራጭ ቢፈልጉ፤ ጥናት በማድረግ የመፍትሔ አቅጣጫዎችን መጠቆም፡፡